*Ethiop.j.lang.cult.commun. June 2026, 11*(1): 285-308

*ISSN: 2518-2919*

*Bahir Dar University-Faculty of Humanities*
https://doi.org/10.20372/ejlcc.v11i1.3181

**Research Article** **Open Access**

# The Moral Philosophy of Sibhat Gebre-Egziabher in Selected Works

**Kehulum Belay Mekonnen[1], Lemma Nigatu Tarekegn [2] & Molla Jembrie Alemneh[3]**

*123Department of Amharic Language, Literature, and Folklore, Addis Ababa Universiy, Addis Ababa Ethiopia*

[2]Department of Ethiopian Languages and Literature, College of Social Science and Humanities, Jimma University, Jimma, Ethiopia

## Abstract

This study rereads and reinterprets two works by Sibhat Gebre-Egziabher, namely Sebategnaw Meleak (The Seventh Angel) and Tikusat (Fever). The analytical approach employed in this study is grounded in concepts of moral philosophy. The justification for the notion of "rereading" lies in the fact that the study advances perspectives that have not been addressed by previous researchers. The absence of prior analyses that examine these works explicitly from the standpoint of moral philosophy constitutes the principal motivation for undertaking this research. The study adopts a qualitative research method, with particular emphasis on the examination and interpretation of moral discourse (morality). It analyzes the moral dilemmas raised in Sebategnaw Meleak and Tikusat, as well as the strategies employed to confront and resolve these dilemmas, using the conceptual framework of Ethical Egoism. The findings indicate that the novels function as vehicles for the author's moral philosophy and confirm that Sibhat Gebre-Egziabher's ethical outlook is fundamentally grounded in self-interest, that is, Ethical Egoism. Sebategnaw Meleak and Tikusat are novels in which social interests are marginalized, human moral virtue is neglected, moral obligations are dismissed, and universal moral good is rendered insignificant. The analysis establishes that egoistic moral reasoning predominates in the ethical vision articulated in the selected works.

**ARTICLE HISTORY**
Received: June, 2025
Revised: January, 2026
Acceptted: February, 2026

**Keywords**:
*Philosophy, Morality, Egoism, Sibhat Gebre-Egziabhe*

**Citation:** Feleke, D. S., Fikre, A., & Merawi, F. M. (2026). The Moral Philosophy of Sibhat Gebre-Egziabher in Selected Works: -. Ethiopian Journal of Language, Culture and Communication, 11(1). https://doi.org/10.20372/ejlcc.v11i1.3181

**CONTACT: Dessalegn Seyoum Feleke email: desephilo@gmail.com**

©2026 The Author(s). Published by Bahir Dar University, Faculty of Humanities.
This is an open access article distributed under the terms of the Creative Commons attribution license (http://creativecommons.org/licenses/by/4.0/), which permits unrestricted use, distribution, and reproduction in any medium, provided the original work is properly cited. The terms on which this article has beenpublished allow the posting of the accepted Manuscript in a repository by the author(s) or with their consent.

# የሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር የግብረ ገብ ፍልስፍና በተመረጡ ሥራዎቹ ውስጥ[1]


## አጠቃሎ

ይህ ጥናት ከሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር ሥራዎች ሁለቱን ማለትም ‹‹ሰባተኛው መልአክ››ን እና ‹‹ትኩሳትን›› ከግብረ ገብ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳብ ፈሮች አንጻር ይፈክራል፤ ይተነትናል፡፡ የአጥኚው የንባብ ቅኝትም የግብረ ገብ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳቦችን ያማከለ ነው፡፡ አጥኚው ባደረገው የንባብ ጥረት መጻሕፍቱን ከግብረ ገብ ፍልስፍና አንጻር የተነተነ አጥኚ አለመኖሩ የዚህ ጥናት አነሳሽ ሰበብ ሆኗል፡፡ ይህ ጥናት ዓይነታዊ የጥናት ዘዴን የተከተለ ሲሆን ትኩረቱም የነገረ ግብረ ገብ (Morality) ሐተታና ፍካሬ ነው፡፡ ጥናቱ በዋነኝነት ስብሐት በሰባተኛው መልአክ እና ትኩሳት ውስጥ ያነሳቸውን የግብረ ገብ ፈተናዎችና ፈተናዎቹን ለማለፍ የተጠቀመባቸውን ፈሮች ከእኔያዊ የምግባር ፍልስፍና (Ethical Egoism) ጽንሰ ሐሳብ አጽናፊ መነጽር ይተነትናል፡፡ በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ የወል (ማኅበረሰብ) ጥቅምና ፍላጎትን አማክለው የሚመጡ ገጸ ባህርያት ቢኖሩም በስተመጨረሻ አሸንፈው የሚወጡት (ስኬታማዎቹ) የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም አስቀድመው የተገኙት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጥናቱ ለመገንዘብ እንደተቻለው መጻሕፍቱ የደራሲው የግብረ ገብ ፍልስፍና ማሄጃ ሲሆኑ የደራሲው ፍልስፍናም የራስ ፍላጎትን መሠረት የሚያደርግ (Ethical Egoism) የግብረ ገብ ፍልስፍና መሆኑን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሰባተኛው መልአክ እና ትኩሳት ማኅበረሰባዊ ፍላጎት ችላ የተባለባቸው፣ የሰው ልጅ ምግባራዊ ጸጋ የተተወባቸው፣ የምግባር ግዴታዎች የተናቁባቸው ብሎም ሁለንተናዊ የምግባር ትሩፋት ‹‹ጉዳይ›› ያልሆነባቸው ልቦለዶች መሆናቸው በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡


**ቁልፍ ቃላት**፤ ፍልስፍና፣ ግብረ ገብ፣ እኔያዊ፣ ሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር

[1] ይህ ጥናታዊ መጣጥፍ ‹‹የግብረ ገብ ሐሳቦች በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች›› በሚል ርእስ ከተሠራው የዶክትሬት ዲግሪ ጥናት በአጭር የወጣ ነው፡፡ አማካሪዎች፤ አየለ ፍቅሬ (ዶ/ር) የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አአዩ፤ ፋሲል መራዊ (ዶ/ር) የፍልስፍና ትምህርት ክፍል፣ አአዩ፡፡

## መግቢያ

ሰው በፈቃዱ ወይም ከፈቃዱ ውጭ በራሱ ወይም በአካባቢው ላይ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽዕኖ የሚደርስበት ፍጡር ነው። እርሱም በተፈጥሮና በአካባቢው ላይ ቀጥተኛ የሆነ እና ያልሆነ ተጽዕኖ እየፈጠረ ይኖራል። ይህ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ መስተጋብር በየጊዜው ውይይትን የሚቀሰቅሱ የምግባር ጥያቄዎች እንዲወለዱ ምክንያት ይሆናል። ዓለማችን የተፈተነችባቸው እና እየተፈተነችባቸው ያሉ ፈተናዎች ሁሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሰው ልጆች ግብረ ገብ ጋር የሚያያዙ ናቸው። እንደ ጠና (2008) ያሉ ምሁራን ከዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች ግብረ ገብ ጉልህ ሥፍራ እየያዘ መምጣቱን ይገልጻሉ። ይህ ያለንበት ዘመን በርካታ የምግባር ጥያቄዎች የሚነሱበት ነው። ሰዎች ከቤታቸው ወጥተው መሥሪያ ቦታቸው ወይም ትምህርት ቤት ወይም የእምነት ሥፍራ እስኪደርሱ ድረስ የነገረ ግብረ ገብ (Moral Philosophy) ጉዳይ የሚሆኑ ተግባራትን ይከውናሉ፣ ሐሳቦችን ያውጠነጥናሉ፣ ውሳኔዎችን ይወስናሉ ወይም በመወሰንና ባለመወሰን መኻል ይዋልላሉ።

በነገረ ገብረ ገብ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ካላቸው ጥበባዊ ሥራዎች ውስጥ ሥነ ጽሑፍ አንዱ ነው። ስለዚህ ነገረ ግብረ ገብን በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ማሰስ እዚህ ጋ ይበቃል ሊባል የማይችል ነገር ነው። ሥነ ጽሑፍ ከተፈጥሮው አንዱ ድንበር ዘለል ተግባራት ያሉት መሆኑ ነው። ሥነ ጽሑፍ የሰውን ልጆች ሁለመና አልፎ የዓለምን እና በዓለም ያሉትን ግዙፍና ረቂቅ ነገሮች የሚፈትሽ ሙያ እንደመሆኑ ድንበር ሳይበጅለት ከሌላ ሙያ ጋር ተማጥቆ አዲስ ዓይነት ዕይታን ማጋራት የሚችል ብዝኃ ዲስፐሊናዊ (Multidisciplinary) ሙያ ነው። ደራስያን በሚፈጥሯቸው ገጸ ባህርያት፣ በሚቀርጽዋቸው ትረካዎች፣ በሚያመጡት መከራከሪያ ግብረ ገብን የተመለከቱ ጉዳዮች ይነካካሉ።

በሌላ በኩል አሁን ያለንበት ዘመን አንድ ጉዳይ ከአንድ አጽናፊ መነጽር ብቻ የሚበየንበት አይደለም። ሥነ ጽሑፍ የሰባኪነት ሚና ብቻ ይዞ የሚቀጥልበት ዕድልም እየቀነሰ መጥቷል። በመሆኑም እያንዳንዱን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ በበይነ ሙያ ጥናት አማጥቆ መፈተሽ አስፈላጊ ነው። በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ የግብረ ገብ ሐሳቦችን ከነገረ ፍልስፍና አንጻር የመረመረ ጥናት አላጋጠመኝም። በተለይ በመረጥኋቸው የአማርኛ ልቦለድ ሥራዎች ላይ ያተኮረ የነገረ ግብረ ገብ ጥናት አላገኘሁም። ይህም ይሄንን ጥናት ለማድረግ ገፊ ምክንያት ሆኖኛል። በዚህ ረገድ ‹‹እንደወረደ›› በሚል ገላጭ የታተሙት የስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ‹‹ሰባተኛው መልአክ›› እና ‹‹ትኩሳት›› የተሰኙትን መጻሕፍት ከነገረ ግብረ ገብ አንጻር መተንተን የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። ሁለቱ መጻሕፍት በዓላማ መር ዘዴ የተመረጡ መጻሕፍት ናቸው። ደራሲው እንደጻሐፊ ሥራዎቹም እንደደርሰት ከነገረ ገብረ ገብ አንጻር ቢጠኑ አንዳች ግኝት ይገኛል ከሚል ዕምነት የተደረገው ይሄ ጥናት የግብረ ገብ ፍልስፍና ጽንሰ ሐሳብን አማክሎ የተጠና ነው። በዚህ አውድ የተመረጠው ጽንሰ ሐሳብ መጻሕፍቱን እንደ ፍልስፍና ማራመጃ፣ ደራሲውን ደግሞ እንደተፈላሳፊ ለመተንተን አገልግሎት ላይ ውሏል።

### ጽንሰ ሐሳቦች

ነገረ ግብረ ገብ አንዱ የፍልስፍና ዘርፍ ነው። ይህም የፍልስፍና ዘርፍ ምግባርን እንደአንድ የፍልስፍና የጥናት መስክ ያጠናል። አጠናኑም የፍልስፍና ሁነኛ መሣሪያ የሆነውን አመክኗዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ሲሆን፣ የግብረ ገብ (Moral) መርሆዎችን የሚያጠይቅ ዘርፍ ነው።

Lewis Vaughn 'Ethics: 'Doing ethics: Moral reasoning and contemporary issues' **በተሰኘ *መጽሐፉ*** 'Ethics is the philosophical study of morality – a rational examination of people's behavior' (2016፡30) ይላል። ምግባር የግብረ ገብ ጥናት ነው። የሰዎችን ግብረ ገብ በአመክንዮ ይመረምራል። ትክክልና ስህተት፣ መልካምና እኩይ ለሚሏቸው ጠባያትና ድርጊቶች መሠረት የሆኗቸውን መርሖዎች ያጠናል። የግብረ ገብ እሴቶችን ምንነት ይመረምራል። ለራሳችን እልፍ ሲልም ለሌሎች ያሉብንን ኃላፊነቶች ይጠይቃል።

በዚህም በዕለት ከዕለት ሕይወታችን ለምንጋፈጣቸው ግብረ ገባዊ ይዘት ያላቸው ውሳኔዎች መሠረት የሚሆነንን ማህቀፍ ይፈልጋል። ለ Peter Singer ምግባር እንዲሁ የማይጨበጡ ጽንሰ ሐሳቦች ጨዋታ አይደለም። ይህንንም ሲያስረዳ፡-

> Ethics is not an ideal system which is all very noble in theory but no good in practice. The reverse of this closer to the truth: an ethical judgment that is no good in practice must suffer from a theoretical defeet as well, for the whole point of ethical judgment is to good practice (2011:2)

ምግባር እንዲሁ በዐየር ላይ የሚንሳፈፍ ተምኔታዊ ዕሳቤ አይደለም እያለን ነው። ይልቁንም አንድ ምግባራዊ መርህ በተግባር ሊገለጥ ያልቻለ እንደሆነ ሲጀምርም የጽንሰ ሐሳብ ግድፈት እንዳለበት የሚያመላክት ነው። ለዚህ መነሻው ደግሞ የግብረ ገብ መርሖዎች አስፈላጊነት የተግባር ሕይወትን መቃኘት መቻል ነው።

## የምግባር ንዑሳን ዘርፎች

ነገረ ግብረ ገብ ወይም የምግባር ጥናት ሰፊ የፍልስፍና ዘርፍ ከመሆኑ አንጻር በተለያዩ ንዑሳን ዘርፎች ተከፋፍሎ ይታያል። ንዑሳን ዘርፎቹ የሚለያዩት ከሚያተኩሩበት ገጽታ፣ ከዘይቤና ዓላማቸው አኳያ ነው። እያንዳንዳቸው የተወሰነን የግብረ ገብ ጽንሰ ሐሳብ፣ ተግባርና አመክንዮ ገጾች ያመለክቱናል። እነዚህ ንዑሳን ዘርፎች በዋናነት ረቂቅ (ዲበ) ምግባር ፍልስፍና (Meta Ethics)፣ ተግባራዊ ፍልስፍና (Applied Ethics) እና የእለት/መመሪያዊ (Normative Ethics) ፍልስፍና ተብለው የሚገለጹ ናቸው። ጽንሰ ሐሳቦቹን ለመረዳት ያግዝ ዘንድ እያንዳንዳቸውን በመሠረታዊነት ደረጃ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

## ረቂቅ (ዲበ) ምግባር ፍልስፍና (Meta Ethics)

ረቂቅ (ዲበ) ምግባር ፍልስፍና የምግባር ጥናት ከሆኑ ቁልፍ ዘርፎች አንዱ ነው። ይህ ዘርፍ በምግባር ጥናት ውስጥ የምንጠቀምባቸውን ጽንሰ ሐሳቦች መሠረታዊ ምንነትን የሚመረምር ነው። ‹‹ዲበ ምግባር ፍልስፍና›› የሚለው አገላለጽም ከሥነ ምግባር የምርምር ጥያቄዎች ከፍ ብሎ ወጥቶ ራሱ ሥነ ምግባርን፣ መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳቦቹን፣ ባሕርይውን፣ የጥያቄዎቹን ትክክለኛነት እና ተገቢነት የሚያጠና መሆኑን የሚያመላክት ነው።

‹‹ዲበ›› የሚለው ቅጽል ከሚታዬው ነገር ያለፈ፣ የተሻገረ፣ የጠለቀና የመጠቀ የሚለውን የሚያመላክት ነው። ዲበ ምግባር ራሱ የምግባር ፍልስፍናን ከውጭ ሆኖ የሚያጠና ወይም የሚመረምር የፍልስፍና ዓይነት ነው።

የምግባር ጥናት ልክና ስህተት፣ መልካምና እኩይ የሆኑ ምግባሮች የትኞቹ ናቸው? የሚለውን የምንለይበት የግብረ ገብ መርህ ምንድን ነው? እያለ ሲጠይቅ፣ ዲበ ምግባር በአንጻሩ እንደ ልክና ስህተት፣ መልካምና እኩይ የተሰኙ ጽንሰ ሐሳቦችን ምንነት ከሥራቸው ይመረምራል።

የግብረ ገብ መርሖዎች እንዴት ያሉ ናቸው? ሲል ይጠይቃል፡፡ ፍጹም ናቸው ወይስ አንጻራዊ? ሲልም ይሞግታል፡፡ Alexander Miller 'contemporary metaethics an introduction' ባለው መጽሐፉ፡- ‹‹Meta ethics is concerned not with what people ought to do, but with what morality it self is›› (2013: 1) ይላል፡፡ የዲበ ምግባር ጉዳይ ‹‹ሰዎች ምን ማድረግ አለባቸው?›› ወይም ‹‹እንደ ምን መኖር አለባቸው?›› የሚል ሳይሆን ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ የሚጥረው ነገረ ግብረ ገብ በራሱ ምንድን ነው? እንዲህ ያለው ፍልስፍና ለምን አስፈለገ? የሚጠናውስ ነገር ርባና አለው ወይ? የማጥኛ መንገዱ ምን ዓይነት ነው? ወዘተ. በሚሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ዲበ ምግባር ከሚያነሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው (Miller 2013፡1-3) የግብረ ገብ እሴቶች ፍጹምና ዓለማቀፋዊ ናቸው? ወይስ በባህልና በግለሰብ የሚበየኑ አንጻራዊ ዕሳቤዎች ናቸው? መልካም እኩይ፣ ትክክል ስህተት ስንል ምን እያልን ነው? የግብረ ገብ ብያኔዎች ከአእምሮ የሚፈልቁ ምክንያታዊ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው ወይስ በነገሮች ላይ ያለን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ መረዳት የሚገልጹ ስሜት አዘል ገለጻዎች ናቸው?

እነዚህና ሌሎች የረቂቅ (ዲበ ምግባር) የምግባር ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄዎችን በሦስት ዋና ዋና ዓይነቶች ጠቅልለን ልናያቸው እንችላለን፡፡ እነዚህም የሥነ ምግባር ጽንሰ ሐሳቦች ከኅልውና (Existance) ጋር የተገናኙ የተያያዥነት (ontological) ጥያቄዎች፣ ከቃላት ትርጓሜ ጋር የሚገናኙ (Semantics) ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የምግባር ጽንሰ ሐሳቦችን የማወቂያ መንገዶችን የሚመለከቱ ሥነ ዕውቀታዊ (Epistemology) ጥያቄዎች ናቸው፡፡

**ተግባራዊ ምግባር (Applied Ethics)**

ሁለተኛው የነገረ ግብረ ገብ ዘርፍ ተግባራዊ ምግባር ነው፡፡ ይህም ጥቅል የሆኑ፣ በፍልስፍናዊ የጽንሰ ሐሳብ ምርምር የሚገኙ መርሖዎችን ተግባራዊ አንድምታ የሚያጠና ዘርፍ ነው፡፡ በዚህም ጥቅል (General) የሆኑ መርሖዎችን ልዩ ልዩ በሆኑ ተግባራዊ የግብረ ገብ ችግሮች እና ፈተናዎች ላይ ለማንበር ይጥራል፡፡ በግልና በማኅበራዊ ሕይወት ላይ የሰው ልጆች የሚያጋጥሟቸው የየዕለትና ዘላቂ የግብረ ገብ አከራካሪና ውስብስብ ጥያቄዎችን ያነሣል፡፡ ነገሮችንም ከፍልስፍናዊ ምግባር (Philosophical Ethics) አንጻር የሚመረምርና ተግባራዊ አቅጣጫዎችን የሚያመላክት ነው፡፡

እንደ አገልግሎት ተኮር (Utiliterianism)፣ ኃላፊነት ተኮር (Deontology) እና ሰብዕና ተኮር (Virtue Ethics) ያሉ ዐቢይ የምግባር ጽንሰ ሐሳቦችን አከራካሪና ተግባር ተኮር በሆኑ እንደ ውርጃ፣ የእንስሳት መብት፣ የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊነት፣ የአእምሮ ህሙማን የመወሰንና የተጠያቂነት ገደብ እንዲሁም የጽኑ ህሙማንን ሕይወት በፈቃድ የማክተም ምርጫ ያሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡

**የዕለት (መመሪያዊ) ምግባር (Normative Ethics)**

የዕለት ወይም መመሪያዊ ምግባር አንዱና ዋነኛው የግብረ ገብ ፍልስፍና ሲሆን፣ የግብረ ገብ ፍልስፍና መሠረታዊ ጥያቄ የሆነውን ‹‹ሰዎች ምን ማድረግ አለባቸው?›› የሚል ጥያቄ የሚያነሣ፣ ሥርዓታዊ የሆነ የድርጊት ማህቀፍን ለማነጽ የሚሞክር የፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡ ስለዚህም ዋነኛ ትኩረቱ ትክክል የሆነውን ስህተት ከሆነው የምንለይባቸውን የግብረ ገብ መርሖዎች (Moral Priniciples) መለየትና መሞገት ነው፡፡ Frankena (1973፡2) እንደሚሉት

የዕለት ወይም መመሪያዊ ምግባር ፍልስፍና የግብረ ገብ ብያኔዎችን ይዘት የሚመለከት ሲሆን ልክና ስህተት የምንላቸውን ፍረጃዎች መስፈርት ይፈልግላቸዋል፡፡

ከዚህ ሐሳብ ጋር ስሙር በሆነ መንገድ ሐሳባቸውን እንደሚያቀርቡት Shafer-Landau (2015:5) የዕለት ምግባር ፍልስፍና ድርጊትን የሚሠሩ መርሖዎችን ለማግኘት የሚጥር የምግባር ፍልስፍና ዘርፍ ነው፡፡ እነዚህ መርሖዎች ከግብረ ገብ አንጻር ትክክልና ስህተት የሆኑትን፣ ግዴታዎችንና የተፈቀዱትን ነገሮች እንዲሁም መልካሙንና እኩዩን ይነግሩናል ይላሉ፡፡ በዚህ የፍልስፍና ዘርፍ ይበልጥ ትኩረት የሚሠጣቸው ፍልስፍናዊ ጥያቄዎች፡- ምንን እንዴት አድርጎ መከወን ነው ልክ? መልካም ሕይወት እንደምን ያለ ነው? ለሌሎች ያለን የግብረ ገብ ግዴታ እስከምን ድረስ ነው? የግብረ ገብ ትክክለኝነት የሚወሰነው በምን መሥፈርት ነው? የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የእለት (መመሪያዊ) ምግባር ሦስት መፈከሪያዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ግዴታን መሰረት ያደረገ (Deontology)፤ ሁለተኛው የርትዕም ምግባር (Virtue ethics) ሲሆን፤ ሦስተኛው እኔያዊ (የግል ጥቅመኝነት) (Ethical Egoism) ናቸው፡፡ ከእነዚህ ከሶስቱ የዚህ ጥናት ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት የሚያተኩረው በእኔያዊ የግብረ ገብ ፍልስፍና ላይ በመሆኑ በዝርዝር እንየው፡፡

**እኔያዊ ምግባር (የግል ጥቅመኝነት) (Ethical Egoism)**

ሰዎች በተፈጥሮ ራስ ወዳድ ናቸው ማለት ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ የሰው ልጅ ድርጊት የግል ፍላጎትን ያስቀደመ ራስ ወዳድነት ያለበት መሆን አለበት የሚል ሙግት ነው፡፡ በRachels እና Rachels፣ 'The elements of moral philosophy' በተሰኘ መጽሐፍ "….ethical egoism is a doctrine that each person ought to pursue his or her own self-interst exclusivly" (2003፡63) የሚል ሐሳብ አለ፡፡ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱን መሻት ብቻ ሊከተል ይገባል እንደማለት ነው፡፡ ስለዚህም፣ የሰዎችን ተፈጥሮ ከማብራራት አልፎ ራስ ወዳድነት ወይም የራስን ጥቅም ከሁሉ አስቀድሞ መመልከትን የግብረ ገብ ዋጋ (Moral Worthiness) መስፈሪያ አድርጎ ይመለከታል፡፡

Rand 'The virtue of selfishness' በሚል ርዕስ በጻፈችው መጽሐፍ "man – every man is an end in himself, not the means to the end of others" (1964፡30) ትላለች፡፡ ይህ አገላለጽ በተለይ Rand እንደምትለው ሁሉም ሰው በራሱ የነገሮች ሁሉ የመጨረሻ ግብ ነው፡፡ ይህም ማለት ማንም ሰው ለሌሎች ግብ መዳረሻ መንገድ መሆን የለበትም የሚል አቋም ነው፡፡

ከወል ጥቅማዊነት በተለየ ሁኔታ የብዙኃን ደስታ ወይም ጥቅም እንደድርጊቶች የግብረ ገባዊነት ዋጋ ሚዛን አድርጎ አይመለከትም፡፡ ይህንን ጉዳይ Sidgwick ሲያብራሩ፣ "Egoism directs me to seek my own greatest happiness; utilitarianism is, the greatest happiness of greatest number" (1874:417) ይላሉ፡፡

የወል ጥቅመኝነት ለብዙኃን የበዛውን ደስታ እንድፈልግ ሲነግረኝ፣ ግላዊ ጥቅማዊነት ግን ለራሴ የበለጠውን ደስታ እንድሻ ይመክረኛል የሚል ሐሳብ ነው፡፡ ሰዎች ምንጊዜም አንድን ድርጊት ከመፈጸማቸው በፊት ማሰብ ያለባቸው ብቸኛ ነገር ‹የድርጊቱ ውጤት ለእኔ ደስታን ይሰጠኛል፤ ጥቅም ያስገኝልኛል?›› ብለው መሆን አለበት የሚል መከራከሪያ ነው፡፡ የግላዊ ጥቅመኝነት ግብረገባዊ ፍልስፍና ሁነኛ ሙግቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

አንደኛ፤ የግልን ጥቅም መሻትና መከተል ከምንም ይበልጥ ምክንያታዊ የሆነ የግብረ ገብ መሰረት ነው፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ሕይወትና ትልም ማስቀደማቸው ተፈጥሯዊና ምክንያታዊ ነው፡፡ የግብረ ገብ ፍልስፍናም ከእውነታው መራቅ እስካልፈለገ ድረስ ይህንን የሰው ልጆች

ተፈጥሮ መቃረን የለበትም። ከዚህ አንጻር የራስን ሕይወትና ፍላጎት በመተው ለሌሎች የሚከፈል መስዋዕትነት ኢ-ተፈጥሯዊና ኢ-ምክንያታዊ ነው። የዚህ ዓይነቱ አመክንዮ ዋነኛ አቀንቃኝ የሆነችው Rand ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፏ ላይ እንዲህ ትላለች፣ "The actor must always be the beneficiary of his action and that man must act for his won rational self-interst. The achievement of his own happiness is man's highest moral purpose" (1964:30)

የRand መከራከሪያ ነጥብ ሰው ከራሱ ሕይወት የበለጠ ወይም የላቀ ግብ ሊኖረው አይችልም ከሚል መነሻ የቀረበ ነው። ሌሎች በሕይወቱ ዋጋ ሊሰጣቸው የሚችሉ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን፤ ሁሉም በእርሱ ሕይወት መቀጠልና የሕይወት ትልም ውስጥ የሚጠቀለሉ ናቸው። ስለዚህም ግብረ ገብ ጠንካራ የሆነ መሰረት ሊኖረው የሚችለው በዚህ የሰው ልጆች መሻት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ብቻ ነው። በመስዋዕትነት ላይ የተመሰረተ ከሆነ ግን ዘላቂነት ያለው እና መሰረቱ የጸና ግብረገባዊነት ሊሆን አይችልም። ለማንና መቼ መስዋዕት እሆናለሁ የሚለው በራሱ በግለሰቡ መሻት ላይ የተመሰረተ ነው አለዚያም ዘፈቀዳዊ ነው የሚሆነው።

ሁለተኛ፤ ሥነ ልቦናዊ ጥቅመኝነት (Psychological egoism) በራሱ ግላዊ ምግባራዊ ጥቅመኝነትን (Ethical Egoism) ይደግፋል። የሰው ልጆች በተፈጥሯቸው የራሳቸውን መሻት ወደ መከተል የሚያዘነብሉ ከሆነ ከዚህ በተጻራሪ የሚወጡ የግብረ ገብ መርሆዎች በሙሉ ከግብዝነት (Hypocracy) የሚመነጩ ናቸው ማለት ነው። Hobbes 'Liviatan' ባሉት ድርሰታቸው ላይ፣ "…For no man given but with intention of good to him self; because gift is voluntary and of all voluntary acts, the object is to every man his own good" (1996:209) ይላሉ።

ስለዚህ ለሌሎች የምናደርጋቸው መልካም ነገሮች በሙሉ ውስጣቸውን ብንመረምራቸው ለእኛ የሚያስገኙት አንዳች ዓይነት ጥቅም በመኖሩ ነው እያለን ነው። ለሌሎች በማድረግ የሚገኝ እርካታን፣ አድናቆትን ወይም ውለታ የሚያስገኘውን ጥቅም አለፍ ሲልም ሀይማኖተኞች የሆንን ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለን ለምናምን ጥሩ መደላድል እንዲሆነን በማሰብ ነው።

ሦስተኛ፤ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት፣ ግለሰቦች በሕይወታቸው በኃላፊነት እንዲወስኑ በተጨማሪም ነጻ እና በራሳቸው የጸኑ እንዲሆኑ ያደርጋል። በተቃራኒው የመስዋዕትነት ግብረ ገብ (altruistic morality) ሰዎች የሌሎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ በተጨማሪም ጥገኛና በሌሎች ተጽኖ ስር እንዲወድቁ የሚያደርጋቸውን ሥነ ልቦናዊ ጠባይ ያላብሳቸዋል። Rand (IBID) መስዋዕትነትን(altruism) እንደሚከተለው ትገልጸዋለች "Altruism holds that man has no right to exist for his won sake, that serves to others is only justification of his existence" (1964:19)። በአንጻሩ፣ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት የሰው ልጆች ስለራሳቸው ብለው እንዲኖሩ ይሞግታል። ለሌሎች መስዋዕትነት የቀረቡ ሳይሆኑ፣ ሕይወትን የሚወድዱ ለራስ መኖርን የሚያውቁ መሆን ይኖርባቸዋል የሚል መከራከሪያ ነው። የመስዋዕትነት ግብረ ገብ ከንቱ ሕይወትንና ኢ-ምክንያታዊ አለዚያም ደግሞ የግብዝነት ተግባር ነው።

አራተኛ፤ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት በሰዎች መካከል እውነተኛ ትብብርን ለመፍጠር የሚያስችል ነው። ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የራስን መሻት ለማሟላት በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ውስጥ ከሌሎች ጋር መረዳዳት ያለውን ጠቃሚነት ይረዳል። በዚህም ከግብዝነት ሳይሆን ከእውነተኛ ምክንያታዊ ፍላጎት የመነጨን ተግባር መተግበር፣ ትብብር እንዲሰፍን ያደርጋል። ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Rachels እንዲህ ትላለች፤ "Ethical egoism does not preclude helping others; if only materials that we should help them when it is in our interst to do so" (2003:64)። መተባበርና መረዳዳት ስለሚያስገኘው ጥቅም ሲሉ ሰዎች ወደዚያ ያዘነብላሉ የሚል ጭምቅ ሐሳብ ያዘለ ነው። እንደዚህ ያለው ለሌሎች የሚጠቅም ነገርን የማድረግ ዝንባሌ

ደግሞ ከግል ጥቅም የመነጨ እንደመሆኑ መጠን ምክንያታዊ ነው፡፡ ግላዊ ጥቅማዊ ምግባራዊነት ከሌሎች ጋር መኖርን፣ መተባበርን፣ የሚቃወም ሳይሆን፣ ይህ ኅብረት ከእውነተኛ ግለ መሻት (Self-interets) የመነጨ መሆን አለበት ነው የሚለን፡፡ ስለዚህም ለግላዊ ጥቅማዊ ግብረገባዊነት የግብረ ገብ ዋጋ መስፈሪያው የግለሰቦች ምክንያታዊ ግላዊ ፍላጎት እናም ያንን ተከትሎ የሚያደርጓቸው ድርጊቶች ናቸው፡፡

# ትንታኔ

## ሰባተኛው መልአክ

መጽሐፉ በ1959 ዓ.ም የተጻፈ ይሁን እንጂ መጀመሪያ በ1992 በሌሎች አርታኢዎች አርትኦት፣ በኋላም በ2000 ዓ.ም ‹‹እንደወረደ›› በሚል ንዑስ ርእስ ታትሟል፡፡ ነገር ግን መጽሐፉ በገጽ ብዛቱ አነስተኛ ሊባል የሚችል በመሆኑ፣ ከዚያ በኋላ ከሌሎች መጽሐፎች ጋር ተዳብሎም ታትሟል፡፡ እኔ የተጠቀምሁት በ2009 ዓ.ም ‹‹ቦርጨቅ›› ከተባለ ሌላ ልቦለድ ጋር ጀርባ ጀርብ ሆኖ የታተመውን እትም ነው፡፡ አራተኛ እትም መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሰባተኛው መልአክ ደራሲው በ1950ዎቹ በፈረንሳይ ሀገር ትምህርት ሊከታተል በሄደበት ጊዜ ያለፈበት ታሪክ ስለመሆኑ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ ለሁለቱም መጽፎች መግቢያ እንዲሆን በጻፈው ሐተታ ላይ አመልክቷል፡፡ መጽሐፉ የያዘው ታሪክም ደራሲው በአንደኛ መደብ ትረካ የሚተርከው ሆኖ በፈረንሳይ ሀገር ተማሪ የነበሩ አፍለኞች ታሪክ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት ሁለቱ የስብሐት መጽሐፎች (ሰባተኛው መልአክና ትኩሳት) ተከታታይነት ያላቸው መሆናቸው በአጥኚው በመታመኑ ነው፡፡ ስብሐት በሰባተኛው መልአክ መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል፤

> ይሄ መግቢያ ለዚህ ለምታነቡት ‹‹ሰባተኛው መልአክ›› ይሁን እንጅ ከዚህ በፊት ላነበባችሁት ‹‹የተኮላሸ ወይም ‹የተበረዘ› እትምና በቅርብ ጊዜ ‹እንደወረደ› ለምናትመው ‹‹ትኩሳት›› ጭምር ያገለግላል፡፡ የሁለቱም ልቦለዶች መቼት ያው በመሆኑ፡፡ ይዘታቸው ይለያያል እንጅ (ገጽ 3)፡፡

በመግቢያው አስረጅነት መሰረት ‹እንደወረደ› የተባለውን እትም በተመለከተ የህትመት ቅድሚያ ያለው ሰባተኛው መልአክ ነው፡፡ ስለዚህም አስቀድሞ ለትንታኔ መምጣቱ ለዚሁ ነው፡፡ በሌላ በኩል ‹ይዘታቸው ይለያያል እንጅ› የሚለው የስብሐት ገለጻ እኔ ከምተነትነው የግብረ ገብ ፍልስፍና ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ እንዲያውም ለእኔ ትንታኔ አመችነትና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው - መጻሕፍቱ፡፡

ሰባተኛው መልአክ በጥቂት ገጾች የቀረበ መጽሐፍ ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ስብሐት እንደ አንደኛ መደብ ተራኪ አንድ ገጸ ባህርይ ነው፡፡ ደግሞ ሌሎች ገጸ ባህርያት አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ያሲን፣ አይሪን እና አየለ ነብርን እርስ በእርስም ይሁን ከሌሎች አስተኔ ገጸ ባህርያት ጋር በተገናኙ ጊዜ የሚመሩባቸውን የስነ ምግባር እይታዎች ፈር እየሰጠሁ አሳያለሁ፡፡

የመጽሐፉ ማጠንጠኛ ነገረ ወሲብ ነው፡፡ ሌሎች ማቅለሚያ ታሪኮች ይኑሩ እንጂ ከታሪኩ መነሻ እስከ መድረሻ ያለው የታሪክ ሰበዝ ነገረ ወሲብ ነው፡፡ ከታሪኩ ላይ እየተጨለፉ ብቅ የሚሉ ገጸ ባሕርያት ወሲባዊ ምልከታቸው፣ ፍላጎታቸው፣ ጠባያቸው እና እምነታቸው በየገጹ ይገለጣል፤ ታሪኩን ወደፊት ያራምዳል፡፡ ወሲብ የፍቅርና የጥላቻ መነሾ ሆኖ ይከሰታል፡፡ ብዙ ጊዜ ገጸ ባሕርያቱ ሁለት ሆነው ስለወሲብ ያቅዳሉ፤ ሶስት ሆነው ወሲብን ይፈጽማሉ፡፡ ሁለት ሆነው ወሲባዊ ሴራ ይጎነጉናሉ፣ ሁለትም ሶስትም ሆነው ‹‹በብልግና›› ውስጥ ይጠመቃሉ፡፡

ሴት የወንዱን ውበት ታደንቃለች፣ ወንድ ወንድን ይመኛል፤ ሴት ከሁለት ወንዶች ጋር መተኛትን ታደርጋለች። ወንድ ከአንድ ወንድና ከአንድ ሴት መሃል ተኝቶ ወሲብ ማድረግን ይመኛል። ደግሞ በሌላ ጎን አንድ ብቸኛ ወንድ አለ፤ ከሚጎነጉነው፣ ከሚሸረበው የማይደርሰው፣ ውስጡን ብቻ እያዳመጠ ከውስጡ የሚጣላ፤ የውስጡ ስሜት ገንፍሎ አእምሮውን የሚያናውጠው።

## አንብሮ አንድ፤ ‹‹የብልግና ውበት የቆሻሻነት ክብር››

እኤያዊ የግብረ ገብ ዕይታ የወል ጥቅም ከሆነው አገልግሎት ተኮር (Utiliterian) ዕይታ መቃረን ነው። ማኅበረሰብ የሚተዳደርበትን ሥርዓት፣ ደንብና ባህል ተወት አድርጎ የግል ፍላጎትንና ደስታን ያማከለ ጉዞን መጓዝ ነው። ከዚህ አንጻር ‹‹የብልግና ውበት የቆሻሻነት ክብር›› የሚለው የስብሀት አገላለጽ የወል ጥቅምን የሚተው የግል ደስታን የሚመኝ ነው። ይህም የስብሐት እኤያዊ የግብረ ገብ እይታ በሁለት አንብሮዎች ላይ የሚንጠለጠል ነው። የመጀመሪያው የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር መቀበል ነው።

ያሲን የራሱ የሆነ ማደሪያ የለውም። ሴቶችን ይወዳል፤ ሴቶችም ይወዱታል። ዛሬ አንደኛዋ ቆንጆ ጋር ያድራል፤ በነጋታው የእሷ ጓደኛ የሆነችን ይዞ ያድራል፤ እሷም ልታሳድረው ትችላለች። በያሲን የመጣ ሴቶቹ አይቀያየሙም። ሁሉንም እኩል እንደሚወዳቸው ያውቃሉ (ገጽ 16-17) ያሲን ለሥርዓት፣ ለወግ ወይም ለይሉኝታ ብሎ የሚያደርገው ነገር የለም። ሁሉንም ነገር የሚያደርገው ወይም ያደረገው ራሱን ስለሚጠቅመው ደስታውን ስለሚያረጋግጥለት ነው።

ለምሳሌ፤ አስቀድሞ ኮሙኒዝምን አነበበ፤ ጥሩ እውቀት ያዘ፤ አሁን ደስታ የሚሠጠው ኮሙኒዝምን እውቀት ሳይሆን፣ ሃይማኖት ማድረግ ነው። ‹‹ያሲን ድሮ ኮሙኒስት ስለነበረ ስለኮሙኒዝም ብዙ እውቀት አለው። ግን አሁን ኮሙኒዝምን እንደዘመናዊ ሃይማኖት ነው የሚቆጥረው›› (ገጽ 23)። ኮሙኒዝምን እንደ ሃይማኖት የያዘው ደስታውን ስለሚያቀርብለት ነው። ኮሙኒዝም ለሁሉም እኩል ደስታን ለመፍጠር፣ እኩል እድልን ለመፍጠር የሚሞክር የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም ይሁን እንጂ፣ ለያሲን ሃይማኖት ነው። እዚህ ጋ ደራሲው ሃይማኖት የሚለውን አገላለጽ የተጠቀመበትን አንድምታ ማየት ያስፈልጋል። ሃይማኖት ቅርበቱ ለስሜት እንጂ ለእውነት አይደለም። አማኝ ሰው መግደል ሃጢአት ነው ሲል፤ ሃይማኖተኛ ግን ‹‹ለሃይማኖቱ ስል ገደልኩ›› ይላልና። ያሲን ቡራኬን እንደሚሰጥ ካህን አንዳችም ወጭ ሳያወጣ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሳይጠየቅ እጁን በኪሱ ከትቶ የትም ቦታ ወጥቶ መግባት የሚችለው ለዚያ ነው።

> እውነተኛ ሊቅ ነው። ማለቴ እውቀትን የሚገበዬው ያንን እውቀት በሥራ ላይ አውሎ ገንዘብ ወይም ስልጣን ወይም ዝና ለማግኜት አይደለም። ለማወቅ ሲል ብቻ ነው። ማወቅ። አለቀ በቃ። እና በጣም አዋቂ ነው (ገጽ 32)።

ትምህርቱን ከተወው ጊዜ የለውም። የመኖሪያ ፈቃድ የለውም። ተምሮ ሥራ የመፈለግ ወይም ወደ ሀገሩ የመመለስና አብዮት የማስነሳት ህልም የለውም። ያን ዓላማ ይዞ አይደለም ፈረንሳይ ውስጥ ያለው፤ ደስታውን ለማጣጣም እንጅ። እርሱ የራሱን ደስታ የሚያገኝበትን መስመር ሁሉ ይከተላል።

> እውነትን በመፈለግ ላይ ነው። እና እውነትን የት እንደሚፈልጋት ታውቃለህ ……. ግብረ ስጋ ውስጥ (ገጽ 33)።

ያሲን ሥራ የለውም፣ ትምህርት አይማርም፣ ንግድ አይነግድም፣ ግን አይቸገርም። ፓስፖርቱ አልታደሰም፣ የመኖሪያ ፈቃድ የለውም፣ ግን አምስት አመት ሙሉ ማንም አልጠየቀውም፤ አልከሰሰውም። (ገጽ 17) አንደኛዋ ሽሚዝ፣ አንደኛዋ ጫማ፣ ሌላኛዋ የውስጥ ልብስ ይገዙለታል። ትናንት ከጉዋደኛዋ ጋር እንዳደረ እያወቀች አንደኛዋ ዛሬን ከእሱ ጋር ወሲብ ለማድረግ አትሽማቀቅም፣ ወይም አትቀናበትም፤ ሁሉንም እኩል እንደሚወዳቸው ሁሉም እኩል ያውቃሉ። ለምን? ያሲን እውነትን የሚፈልጋት ወሲብ ውስጥ ነው፤ ፍለጋው የእለት ከዕለት ኑሮው ሆኗል። የሚፈልገው፣ የሚያምነው የሚደሰተው በወሲብ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ የያሲን ድርጊት ደስታን ለማጣጣም የሚደረግ የወሲብ ፍላጎትን ለማርካት የሚደረግ ነው። በዚህ ዕይታ ያሲን እኔባይ (ኢጎይስት) ነው።

ከዋነኞቹ ገጸ ባህርያት መኻል አይሪን አንዷ ናት፡፡ አይሪን እንግሊዛዊት ናት። የተሳለችው በጣም ቆንጆና ጥሩ ጭንቅላት ያላት ሆና ነው። እያንዳንዱን የምታደርገውን ነገር የምታደርገው እያወቀችው ነው። ነገር ግን የምታደርገው ነገር ሁሉ እሷን እስካስደሰታት ብቻ ነው።

> ስለምንም ነገር ደንታ የላትም። ያሰኛትን ነገር ነው የምትሠራው። ሌሊት ሰባት ሰዓት ስምንት ሰዓት ያሲን ትዝ ያላት እንደሆነ ከአልጋዋ ተነስታ ወደ ቤት ትመጣለች (ገጽ 18)።

በተማሪ ቤት ህግ፣ ወይም በማኅበረሰብ እሳቤ ውስጥ አይደለችም፤ የምታደምጠው ውስጧን ነው። የምታደርገው ለእሷ ደስታ የሚሠጣትን ነገር ብቻ ነው። ደስታ ከሚሠጣት ነገር ወደ ኋላ የምትል አይደለችም። ተራኪው ያሲንን በቤቱ ውስጥ አስጠግቶት በደባልነት እንደሚያኖረው ይገልጻል። (ገጽ 18) አንድ እለት አይሪን እንደለመደችው በሌሊት መጣች፤ ያሲን ግን ቤት ውስጥ አልነበረም፤ ምናልባትም ሌላ ሴት ጋ ሄዷል። በብስጭት ‘I was just in the mood to make love’ ያለችው አይሪን በቀጥታ የፈለገችውን ከመናገር አልፋ ከተራኪው ጋር ወሲብ ለማድረግ እንደምትፈልግ ‹‹ግድ ያሲን መሆን የለበትም፤ ግን ከያሲን እኩል የሚችልበት ወንድ መሆን አለበት›› (ገጽ 18-19) ማለቷ ደስታን የሚሠጣት እስከሆነ ድረስ ያሻትን የምታደርግ በመሆኗ እኔያዊ የግብረ ገብ ተከታይ (ኢቲካል ኢጎኢስት) ሆና እናገኛታለን። በትክክል ኢቲካል ኢጎኢዝምን የምታንጸባርቅ መሆኗን ይበልጥ በአስረጅ እንደግፍ፤

> አየህ በኛ ስልጣኔ ይልቁንም በኔ ቤተሰብ አካባቢ ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት እንደ ሀጢአት ነው የሚታዬው። ስለዚህ ያሲንን ከማወቄ በፊት ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት ሆኖ ባይታዬኝም እንኳዋ እንደ ጥሩ መልካም ነገር አልቆጥረውም ነበር (ገጽ 38)።

በዚህ ንግግሯ ውስጥ ለማስተዋል እንደሚቻለው አይሪን ቤተሰቧ የሚከተለውን ይሉኝታ አፍርሳ የጣለችና በእኔያዊ ፍልስፍና የተጠመቀች መሆኗን ነው። እኔያዊ የግብረ ገብ እይታ ቅድሚያ ለራስ ፍላጎት ነው፤ ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ምን ይለኛል ከሚል ዕይታ የተላቀቀ ነው። ደስታን እስካስገኘላት ድረስ የቤሰተቧ እምነት ወይም ስጋት እሷን እንደማያስጨንቃት ነው የምትገልጸው።

> አሁን ለኔ ግብረ ስጋ ንጹኅ ውብ ነገር ነው። የሕይወት ዳንስ ነው። በማንኛውም ዓይነት ብደንሰው እወዳለሁ። አብሮኝ የሚደንሰው ወንድ ልበ ንጹህ ይሁን እንጅ በኔ ገላ የፈለገውን ቢሠራ ደስ ይለኛል (ዝኒከመአሁ)።

ያሲንን ትፈልገዋለች፤ ከያሲን ጋር ደስ ይላታል፤ ያሲን ያስደስታታል። የሚላትን ሁሉ ታደርጋለች። ያሲን ሁኝ ያላትን ሁሉ ትሆናለች። ያሲን ከተራኪው ጋር ተዋሰቢ ሲላት ትዋሰባለች (ገጽ 34)፤ አየለ ለወሲብ ጠይቋት ፈቃደኛ አልነበረችም። (ገጽ 51) ያሲን ሂጅና አብረሽው ተኚ ሲላት አየለን ‹‹አልጋ ውስጥ በጣም ጥሩ ነኽ›› (ገጽ 79) ትለዋለች። አየለ ግን ‹‹እኔ ለምኛት እምቢ ያለችኝ ሴት ባሏ ሂጂ ስጭው ብሏት መጥታ ስትሰጠኝ ልቀበል አልፈለግሁም›› ይላል። (ገጽ 79)

በሌላ በኩል አየለ ከእኔያዊ የግብረ ገብ እይታ በተቃራኒ የመጣ ገጸ ባህርይ ነው። አየለ በማህበረሰብ ህግ፣ ደምብ፣ ይሉኝታ ጫና ውስጥ ያለ ሰው ነው። ወሲብ እየፈለገ ሴቶችን መጠየቅ ይፈራል። ‹‹አየለ ሴቶች ፊት በጣም አይናፋር ነው›› (ገጽ 15) ያነበበው ነገር ተጽዕኖ ያደርግበታል፤ የርእዮተ ዓለም ልክፍተኛ ነው። ‹‹አየለ ግን የጋለ የተናደደ ኮሙኒስት ነው›› (ገጽ 23) ኮሙኒስት የሆነውም ለኮሙኒዝም ደምቦች በመገዛቱ ነው። ተራኪው አየለን አንጻሪ አድርጎ ያመጣው ይመስላል። እንደእኔ ባይ ገጸ ባህርያት በውስጡ ያለውን እውነተኛ ፍላጎት ከመከተል ይልቅ ‹‹ሰው ምን ይለኛል?›› የሚል ህግ ይከተላል። እኔያዊ ገጸ ባህርያቱ በታሪኩ መጨረሻ አሸናፊ ሆነው ሲቀጥሉ አየለ ተሸናፊ የሚሆነውም ደራሲው የሚከተለው እኔያዊ የግብረ ገብ እይታ ትክክል ነው ብሎ ለመሞገት ያደረገው ይመስላል።

አየለ ነብር ጠንካራ ሰውነት፣ ደልዳላ ማንነት፣ ብስጩነት፣ አንባቢነት፣ ነጭ ጠይነት፣ ደፋርነት የተሞላ ሆኖ ጀምሮ ፍርሃት የሚያርበደብደው፣ ብቸኝነት የሚያጠቃው፣ ሕይወትን የሚጠላ፣ ራሱን የሚያጠፋ ሆኖ ይደመደማል። ተራኪው ያሲንና አይሪን የሚያቀርቡለትን ልቅ የሆነ የወሲብ ጥያቄ በደስታ የሚቀበል ሲሆን፣ አየለ ከመቀበልና ካለመቀበል (ያደረገውን እውነታ በማመንና ባለ ማመን) (ገጽ 82) ሲሟገት ይታያል። ሶስቱ እኔ ባዮች ፍላጎቶቻቸውን ሲያሙዋሉ፣ ለደስታቸው ሲሉ ደስታቸውን የሚያገኙበትን ሁሉ ሲተገብሩ አየለ ግን ከንባብ ካገኘው፣ ከሃይማኖት ከተማረው፣ ማህበረሰቡ ካቀበለው እውነት ጋር ሲሟገት ይታያል፤ የሚፈልገው ግን የማያደርገው ነገር፣ የሚመኘው ግን የማይተገብረው ነገር ለብቸኝነት ለአእምሮ ነውጥ ሲያጋልጠው ይተረካል። ይህም ከፍ ብሎ ለመጠቆም እንደተሞከረው ደራሲው የእኔያዊ ግብረ ገባዊ ፍልስፍናን ልክነት ለማሳየት ያደረገው ይመስላል። ምክንያቱም ተራኪው ከአየለ ነብር ሀገር የመጣ ነው። በተመሣሳይ የትምህርት፣ የሃይማኖት፣ የንባብ እና የእድሜ ደረጃ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው። ነገር ግን የኖረውን ሕይወት እየተረከልን እንደሆነ በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የነገረን ተራኪው (ስብሀት) የእኔያዊ (የኢቲካል ኢጎኢዝም) አቀንቃኝ፤ አየለ ነብር ደግሞ ጸረ አቀንቃኝ ሆነው ተስለዋል። ለምሳሌ፤ አይሪን የወሲብ ቀበኛ፣ ያሲን ወሲብ አምላኪ የሆኑትን ያህል ተራኪውም እምነታቸውን ይጋራል።

> በሕይወቴ እንደዚያች ያለች ሌሊት አሳልፌ አላውቅም። የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር ለመጀመሪያ ጊዜ መገንዘቤና መቀበሌ ነበር (ገጽ 21)።

ይህን የሚለው በአንድ አልጋ ላይ ሶስት ሆነው ሲዋሰቡ ካደሩ ወዲያ ነው። ያሲን ለአይሪን ከስብሀት ጋር አብራው እንድትተኛ፤ ነገር ግን በሩን እንዳትዘጋ ይነግራታል። አይሪን የተባለችውን አደረገች። ስብሀት ከአይሪን ጋር በመዋሰብ ላይ እያለ ያሲን በር ከፍቶ ይገባል። ያለምንም ተጨማሪ ንግግር ልብሱን አውልቆ ወሲባቸውን ይቀላቀላል። ይህ ለእኔያዊ ግብረ ገብ ፍልስፍና ተከታዩ ስብሀት ‹‹የብልግና ውበት የቆሻሻነት ክብር›› ነው። ይሄንንም ተገንዘበ ተቀበለ። የ‹‹ብልግና ውበት›› በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። አየለ ከማህበረሰቡ ወግ አንጻር ሲያስበው ‹‹ነውር›› ሆኖበት አእምሮውን ያናወጠው ‹‹እውነት›› ለተራኪው ምንም ነበር።

> እኔ ሁለታችሁም መሃል እሆን የለ? እሱም ተራውን መሃላችን መሆን ይፈልጋል፡፡ እሱ እኔ ውስጥ ሲገባ አንተ ደግሞ እሱ ውስጥ እንድትገባ ይፈልጋል ….. እሱ (ያሲን) ወንድም ሴትም ይወዳል፡፡ እኔ የምወደድ አይነት ሴት ነኝ፡፡ አንተ የምትወደድ አይነት ወንድ ነህ፡፡ ስለዚህ ሁለታችንንም ይፈልጋል፡፡ አስታውስ፡፡ እሱ እንደኔና እንዳንተ ተራ ሰው አይደለም፡፡ በእሱ አይን እፍረት ወይም ጸያፍ የሚሉት ነገር የለም (ገጽ 36-37)፡፡

አይሪን ናት ተራኪውን የምታግባባው፡፡ ወደ ተሻለ ‹‹ቆሻሻነት ክብር›› እየመራችው ነው፡፡ ‹‹የብልግናን ውበት›› ተገንዝቦ የተቀበለው ተራኪ ይናገራል፤

> ያለችኝን ለሶስት ስናደርገው ታየኝ፡፡ አልቀፈፈኝም፡፡ በሀሳቤ የያሲንን ገላ አየሁት፡፡ ብዙ ጡንቻ የለውም፡፡ ጸጉር የለበትም፡፡ አነስ ያለ ውብ ገላ ነው፡፡ በሐሳቤ አቀፍኩት፡፡ አልቀፈፈኝም (ገጽ 37)፡፡

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው ተራኪው ይሄንን ሐሳብ ሲያመጣ የእኔያዊ ግብረ ገብ ፍልስፍና የተሻለ የግብረ ገብ እይታ ነው የሚል ሙግት ለማቅረብ ይመስላል፡፡ ለዚህም ያመጣው አመክንዮ አየለ በተፈጥሮው ዝንባሌው ወደ ወንዶች መሆኑን በያሲን በኩል ይገልጻል፡፡

> ግን በሰው ልጆች መካካል በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ህዝብ አንዳንድ የተለዩ ወንዶች ይገኛሉ፡፡ ከአፈጣጠራቸው ይሁን ወይስ ከአስተዳደጋቸው ወይስ ከሁለቱ ይሁን እንጃ ገላቸው እና መንፈሳቸው ወንድን እንጅ ሴትን አይወድም …. አየለ ከእንዲህ አይነቶቹ ሰዎች አንዱ ነው፡፡ ታዲያ እጣው ሆኖ ኢትዮጵያ ውስጥ ተወለደ (ገጽ 30)፡፡

ከዚህ በኋላ ጠንካራ፣ ደፋርና ኩሩ የነበረው አየለ ሰቀቀተኛ፣ ፈሪና ተሽኮርማሚ ሆኖ አእምሮው ተናውጦ የሚመጣበት አጋጣሚ ይሆናል፡፡

> እኔንጃ ምን እንዳደረኳቸው፡፡ እስኪ ምን በደልኳቸውና እንዲህ ይሉኛል? እስኪ ምኔ ነው ሆሞ? ምኔ ነው ጆርናሊስት? አንተና ያሲን ታውቁኛላችሁ፡፡ መጀመሪያ ያሲን የነገራቸው መስሎኝ ነበር (ገጽ 52)፡፡

አየለ በድንገት ወደዚህኛው የአእምሮ ሁኔታ ተቀይሮ ይመጣል፡፡ በንግግሩ ውስጥ ምን እንደቀየረው ማየት የሚቻል ይመስላል፡፡ ‹‹አንተና ያሲን ታውቁኛላችሁ›› የሚለው ሌሎች ከየት አውቀውብኝ ሊሳለቁብኝ ቻሉ ለማለት ይመስላል፡፡ ቀጥሎም ‹‹መጀመሪያ ያሲን የነገራቸው መስሎኝ ነበር›› ይላል፡፡ ግንኙነቱ የነበረው ከያሲን ጋር ነበር፡፡ ስለዚህ ያሲን ያወራብኝ መስሎኝ ነበር ነው፡፡ ለዚህ አስረጅ በሌላኛው የመጽሐፉ ገጽ ይገኛል፡፡ አየለ የአእምሮው ሁኔታ መለስ ብሎለት የኑዛዜ ያህል ለተራኪው እያወራ ነው፡፡

‹‹ድርጊቱ አያሳፍርም መንገሩ ነው የሚያሳፍረው›› (ገጽ 81) ብሎ ይጀምርና ከብዙ ማማጥ በኋላ፣

> እንግዲህ የሚያሳፍር ቦታ ደረስኩ፡፡ እንደሌሎቹ የሀገሬ ልጆች ብትሆን ይሄንን ነገር አልነግርህም ነበር፡፡ አየህ ያሲን መብራቱን አጠፋና አልጋዬ ውስጥ ገባ፡፡ እንዴት ልበልህ? በቃ …ሆነ ነገሩ (ገጽ 82)፡፡

‹‹እንደሌሎቹ የሀገሬ ልጆች ብትሆን ይሄንን ነገር አልነግርህም ነበር›› የሚለው የአየለ ንግግር አንድ ደጋፊ እየፈለገ ያስመስለዋል፡፡ ይህም ሆኖ አየለ በጨለማ መብራት አጥፍቶ ማድረጉ አያሳፍርም፤ ይሄንን በግልጽ ማሳወቁ ነው የሚያሳፍረው ይላል፡፡ አየለን እያስጨነቀው ያለው እየገዛው ያለው ደምብ ነው፤ ያደገበት ማህበረሰብ ወግና እሴት ነው፡፡ በጨለማ ሲያደርገው ያልቀፈፈው እሱን ለመሰለ ሰው ለመንገር ግን አስጨነቀው፡፡

## አንብሮ ሁለት፤ እንደያሲን ቅዱስ

ከላይኛው አንብሮ ጋር ተያያዥነት ያለው ‹‹ውበትም እውነትም›› የሆነው አንብሮ ደግሞ እንደ ያሲን ቅዱስ መሆን ነው፡፡

ያሲን ከሁለት ሀበሾች ጋር ትውውቅ እንዳለው በመጽሐፉ ላይ በግልጽ ተጽፏል፡፡ ከአየለና ከተራኪው ጋር፡፡ ያሲን ሁለቱንም ወንዶች ለወሲብ ጠይቋቸዋል፡፡ ተራኪው ‹‹አልቀፈፈኝም፡፡ ግን ከዚህ በፊት ስለ ወንድ እንዲህ አይነት ሀሳብ መጥቶልኝ አያውቅም›› ይላል፡፡ ‹‹የብልግናን ውበት የቆሻሻነትን ክብር›› ተገንዝቧል ተቀብሏል፡፡ ሁለተኛው አየለ ነው፡፡ አየለ የያሲንን ግብዣ ተቀበሏል፡፡ ግን ከህሊናው ተጣላ፡፡ ራሱን አጠፋ፡፡

ይህንን ለማስረዳት ይመስላል ደራሲው በአይሪን በኩል የወል (የማህበረሰብ የሆነውን) የቅድስና እሳቤ በማፍረስ አዲስ የቅድስና እሳቤ ለማሳዬት የሚሞክረው፡፡ የያሲንና ተራኪው እንዲሁም የያሲንና አየለ አገናኝ (ድልድይ) የሆነችው አይሪን ያሲንን ‹‹ቅዱስ›› ብላ ስትጠራው ‹‹የሮማው ጳጳስ ይሰሙሽና›› ብሎ ሐሳቧን እንድትቀጥል በፌዝ ማስፈራራት ለሚጋብዛት ተራኪ እንዲህ ትተነትናለች፡፡

> እኔ የእነሱን አይነት ቅዱስነት ከቅዱስ አልቆጥረውም [...] እነሱ ሰውን ቅዱስ የሚሉት ምድራዊውን ሕይወት የካደ እንደሆነ ነው፡፡ እኔ ግን ሰውን ቅዱስ የምለው ምድራዊውን ሕይወት በሙሉ ልብ የተቀበለ እንደሆነ ነው (ገጽ 35)፡፡

አይሪን ቅዱስ የምትለው እንደያሲን ያለውን ነው፡፡ በድንግልና መኖርን የሚጠላ ነው፡፡ የማይቀበል፡፡ ትዳርን የማይፈልግ ነው፡፡ በአንድ መጽናት ስህተት ነው ብሎ የሚያምን ነው፡፡ እሱም ሰው ‹‹ለሶስት የሚደረግ ግብረ ስጋ በጣም ስሜት ይሰጠዋል›› (ገጽ 34) እንደ ያሲን ቅድስና ላይ የደረሰ ሰው ሕይወትን መኖር ይጀምራል፡፡ በህግ፣ በእሴት፣ በሃይማኖት ድንጋጌዎች ሳይሆን ‹‹ቆሻሻነት›› ውስጥ ‹‹ውበትም እውነትም እንዳሉበት›› (ገጽ 33) ያውቃል፡፡

> ጥልቅ ሕይወትን የኖረ ይመስለዋል፡፡ አየህ ለእሱ እንደሚታዬው አንድ ብቻህን መኖር ትልቅ ዕድል ነው፡፡ ሁለት ብቸኛ ተገናኝተው ለጥቂት ደቂቃዎች በግብረ ስጋ ብቸኝነታቸውን ሲያሸንፉና ሁለቱ ብቻ ሲዋሃዱ ገነት ማለት ነው፡፡ ከሁለት አልፎ ሶስት ሲሆኑ ደግሞ ከዚያም ይበልጣል (ገጽ 34)፡፡

የያሲን ቅድስና እኔያዊ ፍልስፍና ነው፡፡ እኔ ባዮች በማህበረሰብ እሴቶች፣ ደንቦች፣ ህግጋትና ስርዓቶች ላይ የሚያምጹ ናቸው፡፡ የራሳቸውን ደስታ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ለራሳቸው ደስታ የሚታትሩ ናቸው፡፡ ራሳቸውን እስካልጠቀማቸው፣ የራሳቸውን ፍላጎት እስካላሟላላቸው ድረስ ለሌሎች አንዳች ተግባርን አይተገብሩም፡፡ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ‹‹እኔ›› እና ‹‹ለእኔ›› የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህን እኔ ባዮች ከማህበረሰቡ እሴቶች አንጻር ያየናቸው እንደሆነ ብቸኞች ናቸው፡፡ አይሪን ስለያሲን ቅድስና ስታወራ የምትተነትነው ይሄንኑ ነው፡፡ ‹‹አንድ ብቻህን መኖርህ ትልቅ

ዕድል ነው›› የሚለው ንግግሯ ከያሲን የወረሰችውና የምታምንበት ብላም ተራኪውን ለማሳመን ያነሳችው ነው፡፡

ግብረ ገብ ነገሮች ከራስ አንጻር የሚታዩበት እንጂ ለብዙሃኑ ተብሎ ግለሰቦች የሚጨቆኑበት አይደለም፡፡ ለእኔ ባዮች ትክክለኛ ግብረ ገብ ለብዙሃኑ ደስታ ሲባል ጥቂቱን መጨቆን ሳይሆን ለግለሰብ ደስታ ተብሎ የብዙሃኑን እምነት (እሴት) መናድ ነው፡፡ ወይም ከነጭራሹ እሴት የሚባል የለም፤ የግል ፍላጎትና ደስታ እንጂ ብሎ ማመን ነው፡፡ አንድ የእኔያዊ ግብረ ገብ አቀንቃኝ በብቸኝነት መኖሩ ትልቅ ዕድል ነው፡፡ ደግሞ ሌላ እሱን የመሰለ ሲገኝ ገነት ነው፤ ሶስተኛ እነሱን የመሰለ ሲገኝ ከገነትም ይበልጣል፡፡ ያንን መረዳት ወይም ማየት የሚችለው እንደ ያሲን ያለ ቅዱስ ነው፡፡ (ዝኒከመአሁ)

> እዚህ አልጋ ውስጥ ለሶስት በምንተኛበት ጊዜ ለእኔና ላንተ የሚታየን አንድ አይነት ግብረ ስጋ ብቻ ነው፡፡ ለእሱ (ያሲን) ግን ከዚያ በላይ ብዙ ሌላ ነገር፤ ብዙ ውብ ነገር ይታየዋል [...] እንደ ያሲን ቅዱስ ብሆን ምናልባት ይታየኝ ነበር (ገጽ 34-35)፡፡

ይህ የአሪን ምስክርነት ነው፡፡ ያሲን ቅዱስ ነው፡፡ ቅዱስነቱም ለማንም ብሎ ሳይሆን ለእርሱ ፍላጎት ሲል የሚኖር በመሆኑ ነው፡፡ እኔያዊ የግብረ ገብ ፍልስፍና የማይቀበሉቱ ወይም የማያውቁቱ ወይም በሌላ ዓይነት የግብረ ገብ ዕይታ ውስጥ ያሉ ሰዎች ለብቻቸው መቆም አይችሉም፡፡ ያሲን ግን ይችላል፡፡ ምክንያቱም፤

> እውነተኛ ሊቅ ነው፡፡ ማለቴ እውቀትን የሚገበየው ያንን እውቀት በስራ ላይ አውሎ ገንዘብ ወይም ስልጣን ለማግኜት አይደለም፡፡ ለማወቅ ሲል ብቻ ነው፡፡ ማወቅ፡ አለቀ በቃ፡፡ እና በጣም አዋቂ ነው [...] ማወቅ ስልህም አጠናቆ ነው፡፡ በፊት ኮሙኒስት ነበር፡፡ ግን ሰላማዊ በመሆኑ ከኮሙኒስቶች ጋር አልተስማማም፡፡ አጉል እምነትም የለው፡፡ ሃይማኖትም የለው (ገጽ 32)፡፡

ከዚህ ቀደም ‹‹ኮሙኒዝምን እንደ አዲስ ሃይማኖት ነው የሚያየው›› ከተባለው አገላለጽ ጋር የሚሰምር አገላለጽ ነው፡፡ በዚህኛው የአይሪን ንግግር ውስጥ ቁልፍ የደራሲውን የምግባር ፍልስፍና ማግኘት የተቻለ ይመስላል፡፡ ደራሲው በመጽሐፉ የመግቢያ ገጾች መንፈሳውያን፣ ወታደራውያን እና ኢኮኖሚያውያን ይህችን ዓለም (ገጽ 4) በራሳቸው መንገድ ይመሯታል፤ ይገዟታል፡፡ ይቦጠቡጧታል ይላል፡፡ እነዚህ ሶስት ሃይላት ዓለምን እና ነዋሪዎቿን እንዳሻቸው ለማድረግ የሚያስችላቸውን ህግ ያወጣሉ፤ ደንብ ይደነግጋሉ፣ ሥርዓት ያበጃሉ፣ ሥነ መለኮት ይቀነብባሉ፡፡ ያሲን ሊቅ እና ቅዱስ የሚባለው ለህግ፣ ለደንብ፣ ለሥርዓትና ስነ መለኮት የማይገዛ ይልቁንም ራሱን የሚያዳምጥ ለራሱ ብቻ ቅድሚያ የሚሰጥ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ኮሙኒስት ነበር፤ ነገር ግን እንደኮሙኒስቶች አመጸኛ ባለመሆኑ (ሰላማዊ በመሆኑ) ከኮሙኒስቶች ጋር አልተስማማም፡፡ አጉል እምነት የለውም፤ በጉልበት ጫና ማድረግን አይቀበልም፡፡ ሃይማኖትም የለውም፣ በሰማይ እንዲህና እንዲያ ያለ ሕይወት ይጠብቅሃል እያለ ጨቋኝ ደምብ አይደነግግም፤ የተደነገገውንም አይቀበልም፡፡

አይሪን እንደምትመሰክረው ያሲን አሁን ራሱን ነጻ ያወጣ የእኔያዊ ግብረ ገባዊ ፍልስፍና አራማጅ ነው፡፡ ነጻ ሰው፣ ቅዱስ ሰው በመሆኑም ‹‹እውነትን በመፈለግ ላይ ነው›› (ገጽ 33)፡፡ እውቀትን ለማወቅ ሲል ጠንቅቆ እንደሚያውቅ የሚገለጽለት ያሲን በእውቀቱ ምክንያት ገንዘብ የማግኘት ምኞት እንደሌለውም ይነገርለታል፡፡ በእውቀቱ ምክንያት ስልጣን እንዲሰጠው እንደማይፈልግም ተነግሮለታል፡፡ ያሲን የሚፈልገው እሱ አይሪን ውስጥ ሲገባ ተራኪው እሱ

ውስጥ እንዲገባለት ነው፡፡ (ገጽ 36) ወይም እኩለ ሌሊት ላይ ወደ አየለ ቤት አምርቶ ‹‹ደክሞኛል፣ በእግሬ ከምሄድ እዚህ አድሬ ባጫወትህ ምናለ?›› (ገጽ 82) ማለትን ነው የሚፈልገው፡፡ ምክንያቱም ያሲን ቅዱስ ስለሆነ ‹‹እውነት››ን የሚፈልጋት ግብረ ስጋ ውስጥ ነው፡፡

> አየህ በእኛ ስልጣኔ ይልቁንም በኔ ቤተሰብ አካባቢ ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት፣ እንደሃጢአት ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህ ያሲንን ከማወቂ በፊት ግብረ ስጋ እንደ አሳፋሪ ውድቀት ሆኖ ባይታየኝም እንኳ እንደ ጥሩ መልካም ነገር አልቆጥረውም ነበር (ገጽ 38)፡፡

አይሪን ናት አሁንም ምስክርነት የምትሰጠው፡፡ የያሲን ቅድስና እውነተኛውና ትክክለኛው የግብረ ገብ ፍልስፍና መሆኑን እየሰበከች ነው፡፡ ለተራኪው ስለያሲን ቅድስና ስትናገርም ራሷን እማኝ አድርጋ ነው፡፡

‹‹አንድ ብቻህን መኖር ትልቅ አድል ነው›› (ገጽ 34) የሚለው ገለጻ እዚህ ጋ ይመጣል፡፡ አይሪን ግብረ ስጋ አሳፋሪ ውድቀት ነው ብሎ በሚያምን ቤተሰብ ውስጥ እያደገች ‹‹አሳፋሪ ውድቀት ነው›› አትልም ነበር፡፡ ግን ግብረ ስጋን እንደመልካም ነገር አትቆጥረውም ነበር፡፡ ‹‹አሳፋሪ ውድቀት›› የሚለው የቤተሰቧ አስተምህሮ የተጫነባት የእሴት ጭነት መሆኑን እየተናገረች ነው፡፡ የእኔያዊ ግብረ ገባዊ እይታ በውስጧ የነበረ መሆኑን፣ ነገር ግን ያንን ፍልስፍናዋን መኖር የጀመረችው ከያሲን ጋር ከተገናኘች በኋላ መሆኑን እየገለጸች ነው፡፡ እሷ ከያሲን ጋር በመገናኘቷ ገነት ስለመግባቷ ትገልጻለች (ገጽ 34)፡፡

ይህ አይሪን እየመሰከረች ያለችው ወሲብን ያማከለ የግብረ ገብ ፍልስፍና በያሲንም ይገለጻል፡፡

> የእናንተ የሀበሾች ኑሮ ወንድ ለወንድ መዋደድን በጣም ከመጥላቱ፣ ከመናቁ የተነሳ ተራው ሀበሻ ወንድ ለወንድ መዋደድን እንደ ትልቅ ሃጢአት፣ እንደዋና ውርደትና እንደ ቀፋፊ እፍረት ይቆጥረዋል፡፡ እውነቴን አይደለም? (ገጽ 30)፡፡

በሀበሻ ልማድ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ሃጢአት ነው፡፡ አሳፋሪ ነው፡፡ ቀፋፊ ነገር ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያውያን ግብረ ገብ ነው፡፡ ያሲን ስለኢትዮጵያውያን ግብረ ገብ ያጠናውን ጥናቱን ወይም ያወቀውን እውቀነቱን የሚነግረው ለኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ይህ ኢትዮጵያዊ ደራሲው (ተራኪው) ነው፡፡ ተራኪው የያሲንን ቅድስና (እኔያዊ ግብረ ገባዊ ፍልስፍናን) ይቀበላል፡፡ እንደ ያሲንም እውነትን ወሲብ ውስጥ መፈለግ ይጀምራል፡፡ ተራኪውም አየለም ውስጣቸውን ያውቃሉ፡፡ በሁለቱ መካከል የመጨረሻው ሰዓት ወይይት ላይ ይህ ይነሳል፤

> ከአጭር ዝምታ በኋላ ‹‹ይመስለኛል ይሄ ያሲን እንደኔና እንዳንተ ተራ ሰው አይደለም›› አለኝ
>
> ‹‹አይደለም›› አልኩት
>
> ‹‹የእውቀቱን ስፋትና ጥልቀት ማለቴ አይደለም›› አለኝ
>
> ‹‹አውቃለሁ›› አልኩት
>
> ‹‹ምን ታውቃለህ?››
>
> ‹‹ልቡ ንጹህ ነው››

‹‹ኧረ ከሱ ሌላ?››

‹‹ከሴቶችም ከወንዶችም ጋር ይተኛል››

‹‹ይሄን ድሮም ታውቅ ነበር?››

‹‹አዎን››

‹‹ታዲያ ልጁ አይቀፍህም?››

‹‹በጭራሽ!››

‹‹አትንቀውም?››

‹‹ቢቻለኝ ኖሮ እኔም እንደሱ መሆን በፈለግሁ››

‹‹ይገርማል፡፡ በጣም በጣም Broad Minded ነህ›› አለኝ (ገጽ 79-80)፡፡

ሁለቱም ውስጣቸውን ያውቃሉ፡፡ ተራኪው በነያሲን ቅድስና ውስጥ ነው፡፡ ልበ ሰፊ ነህ የተባለው ለዚያ ነው፡፡ ተራኪው ነገሩ እንደማያሳፍር ሲያረጋግጥለት ነው አየለ ለኑዛዜ የሚነሳው፡፡ አየለ የእነያሲን ቅድስና አልሰረጸውም፡፡ የነያሲን እኔያዊ የግብረ ግብ እይታ ሊዋጥለት አልቻለም፡፡ እሴት፣ ስርኣት፣ ሃይማኖት ችሎ ሊለያቸው አልቻለም፡፡ የህሊና ወቀሳውን ሊቋቋም አልቻለም፡፡ ራሱን አጠፋ፡፡ ተራኪው ከአየለ ጋር የአንድ እሴት፣ የአንድ ሃይማኖት፣ የአንድ ባህል ውጤት ሆኖ ሳለ እንደአየለ የህሊና ወቀሳ ያልደረሰበት፣ ያልፈረው ያልተሸማቀቀው፣ ራሱን ያላጠፋው እኔያዊ የግብረ ገብ ፍልስፍና አራማጅ በመሆኑ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሰናል፡፡

## ትኩሳት

ሰባተኛው መልእክ የደራሲውን የግብረ ገብ ፍልስፍና የሚያሳይ ነው፡፡ ትኩሳት ደግሞ ወደዚያ ፍልስፍና ያደረሰውን መንገድ የሚተነትን ነው፡፡ እዚህኛው ትንተና ላይ በግልጽ የደራሲው ፍልስፍና ለማለት ያስቻለ ሀቀ አለ፡፡ ተራኪ ሆኖ የቀረበው ሰው ራሱ ደራሲው ስለመሆኑ፣ ታሪኩም ያለፈበት፣ በልቦለዱ ውስጥ ያለው የገጸ ባህርይው እምነትና አቋምም የራሱ መሆኑን በግልጽ ስለጻፈው ነው፡፡ ‹‹ዝክር›› ብሎ በትረካው ማለቂያ ላይ በጨመረው የእጅ ጽሑፉ ደራሲው እንዲህ ይላል፤

> እሱ ራሱ (ደራሲው) ለባህራም እንደነገረው ለሀገርና ለህዝብ ብሎ እንኳን እድሜውን ሙሉ ሊሰዋ ቀርቶ ያንድ ሰዓት እንቅልፍ አይከፍላቸውም፡፡ ምክንያቱም እሱ ውስጥ ያደረው ልዝብ የተረት ተረት ዛር እንጅ በሳጥናኤል ኮከብ ብርሃን የሚመራው ቆራጡ የባህራም ውቃቢ አይደለም (ገጽ 259)፡፡

ይህ ደራሲው ስለራሱ እምነት የተናገረው የኑሮ ፍልስፍናው ነው፡፡ በሰባተኛው መልእክ የተጠቀመው ‹‹የብልግና ውበት›› ‹‹የያሲን ቅድስና›› በትኩሳት ውስጥ ሰፍቶና ተብራርቶ ይቀርባል፡፡ በትኩሳት ውስጥ ሁለት ወገን አለ፡፡ የማህበረሰብ መለወጥ፣ የማህበረሰብ መሻሻል የሚገደው እና የግል ደስታን መፈልግ ብቻ የሚገድደው ወገን፡፡ ሁለቱም የየራሳቸውን እውነትና እምነት እየኖሩም፣ እየተናገሩም ሙግታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ደራሲው እሱ ያለበትን

የግል ደስታ አሳዳጅ ወገን፣ ልዝብ የተረት ዛር ሲል ይገልጸዋል፡፡ እነባህራም ያሉበትን ወገን ደግሞ ‹‹በሳጥናኤል ኮከብ የሚመራ›› ይለዋል፡፡

ልዝብ የተረት ዛሩ ያናገረውም፣ ያኖረውን ሕይወት ‹‹በነጻነት ተኑሮ፣ በነጻነት ተጽፎ፣ በነጻነት የታተመ›› (ገጽ 259-260)›› ሲል ይገልጸዋል፡፡ ይህ የግል ደስታን የመሻትና የማሳደድ ‹‹የመቆሸሽ ውበት›› ፍልስፍናን ሲጽፍ ይታተምልኛል ብሎ አምኖ እንዳልነበረ በዝክሩ ላይ ይጠቁማል - ስብሐት፡፡ ሊታተምልኝ ይችላል የሚል እምነት እንዳያዳብር ያደረገው ደግሞ ‹‹ግብዝነትን እንደ ግርማ›› የለበሰው (የኢትዮጵያዊያን) ባህላችን ነው የሚል እምነት አለው፡፡

ስብሐት ትክክለኛው የግብረ ገብ እይታ ለማህበረሰብ አብዮት መሰዋት ሳይሆን፣ የግልን ጥቅም ማስጠበቅ፣ የግል ደስታን ማሳደድ ነው የሚለውን አመክንዮ በትኩሳት ውስጥ ይበልጥ ያብራራዋል፡፡ ይህንን የግብረ ገብ እይታውን ያብራራበት ይህ መጽሐፉ ታትሞ ለአንባቢያን በመድረሱም ደስታውን ይገልጻል፡፡ ስለዚህም ነው እንዲህ የሚለው፤

> ያን ጊዜ ግብዝነትን እንደ ግርማ ሞግስ ለብሶ ‹‹ባለህበት ሂድ›› ስልት የሚንጎማለለው ባህላችን ምናልባት እርምጃውን ይቀይር ይሆናል፡፡ ምናልባት ይሆን ይሆናል (ገጽ 259)፡፡

በሰባተኛው መልአክ ያየናቸው ዋና ዋና ገጸ ባህርያት የእኔያዊ ግብረ ገብ ሐሳብ አንጸባራቂ ወይም ጠባቂ ሆነው ነው፡፡ እየለን እና ሌሎች ጥቂት ገጸ ባህርያት ከእኔያዊ የግብረ ገብ እይታ ውጭ ያለው (እሴት፣ ሥርዓት፣ መስዋዕትነት፣ እምነት) ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የግብረ ገብ እይታ ልክ አለመሆኑን ለማንጸር እንዲያስችሉ ሆነው ተስለዋል፡፡ በሕይወታቸው ደስታን ሲያጡ፣ በስተመጨረሻም ራስ ማጥፋትን አማራጭ ሲያደርጉ እናያለን፡፡ ይህ ውጤቱ የተገለጸበት መጽሐፍ ነው፡፡

በትኩሳት ውስጥ ሶስት ያህል ኢራናውያን ገጸ ባህርያት ይመጣሉ፡፡ ልክ እንደያሲን ሁሉ ቀድሞ የመጣው ገጸ ባህርይ ኢራናዊ ባህራም ይሆናል፡፡ ጀምሽድ ቀጥሎ ይመጣል፡፡ ከዚያም ማኑ ይመጣል፡፡ እነዚህ ሶስት ኢራናውያን ከደራሲው ጋር ይገናኛሉ፡፡ የተለያየ የሕይወታቸው ገጽታም በደራሲው በኩል ይተረክልናል፡፡ የባህራምና የያሲን ሕይወት ተናባቢ መሆኑ ግን በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ቀጣዮቹን የታሪክ አንጓዎች እንመልከት፤

> ከፈረንሳይ መንግስት እንደኛ እስኮላርሽፕ የለውም፡፡ ከሀገሩም ገንዘብ የሚልክለት የለም (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 16)፡፡
>
> ባህራም ስኮላርሽፕ የለውም፡፡ በቤቶቹ ገንዘብ ነው የመጣው፡፡ ግን ቤቶቹ ሳንቲም ከላኩለት ይኸው ስድስት ወር አለፈ፡፡ ምን እንደነካቸው አይታወቅም፡፡ ታዲያ እሱ ሳንቲም ሳያገኝ እኛ በወር 600 ፍራንክ እየበላን ከእኛ እኩል ካፌ እየገባ ይወጣል፤ ከእኛ እኩል ሲኒማ ይገባል፤ ከእኛ እኩል ፓርቲ እየመጣ ይደንሳል፤ ሴት ያሳድዳል (ትኩሳት ገጽ 11)፡፡
>
> ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚያግዘው ያገኛል፡፡ ሸሚዙ ሲያረጅ አንዷ ሸሚዝ ትገዛለታለች፡፡ ጫማው ሲያልቅ ሌላዋ ጫማ ትገዛለታለች፡፡ ክረምት ገብቶ ሊበርደው ሲጀምር አንዷ ሹራቧን ትሰጠዋለች፡፡ ይቀበላል (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 17-18)፡፡

> ከማውቃቸው ሰዎች ከአብዛኛዎቹ አምስት አስር ሃያ ፍራንክ ተበድሪያለሁ ይመስለኛል። አሁንማ ስንት ፍራንክ ከስንት ሰው እንደተበደርኩ እርግጠኛ አይደለሁም። ሰዎቹን በቀን በቀን አገኛቸዋለሁ። በቅርብ እመልስልሃለሁ እያልኩ ነበር የተበደርኳቸው። እና ሳያቸው አፍራለሁ (ትኩሳት ገጽ 67)።

> ያሲን ግን ያለፈቃድ ፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ሲኖር አምስት ዓመት አልፎታል። ልዩ የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠው ባእድ ሰው ፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ስራ ሊይዝ አይችልም። ያሲን ግን ሥራ በየጊዜው ይይዛል። ሁለት ሶስት ወር ይሰራና ይተወዋል (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 17)።

> ልክ አራት ሳምንት እንደሰራ ስራው አለቀ። አሰናበቱት። ቅዳሜ ነበር። ባለውለታ አለቃውን አመስግኖ ሲሰናበታት ራት ጋበዘችው። ቤቷ አመሸ። ሲያያት እርጅና አፋፍ ላይ ደርሳለች። ወንድ ካገኘች ብዙ ጊዜ ሳይሆናት አይቀርም። ከእንግዲህ ማግኘቷንም እንጃ። ሲያስብ ጊዜ እሷ ደግ ባትውልለት ኖሮ ይሄን ጊዜ በራብ ሞቶ ነበር። ሆን ብሎ ብዙ ወይን ጠጣና ሰከረ። አብሯት አደረ። (ትኩሳት ገጽ 99)።

በዚህ ብቻ ገለጻ አይደለም የሁለቱ ታሪክ የሚናበበው። ወይም ሁለቱም ኢራናውያን በመሆናቸው፤ ሁለቱም ኮሙኒስት በመሆናቸው ብቻም አይደለም የሚናበቡት። አይሪን ስለያሲን የምትሰጠው የስሜት ምስክርነትና ሲልቪ ስለባህራም የምትገልጸው የስሜት ምስክርነትም ጭምር እንጅ።

> እንደ አገልጋዩ ልትቆጥረኝ ትችላለህ። እስካሁን ያገኘሁት ሰው ሁሉ ሲያገለግለኝ ነው የኖርኩት። ለወላጆቼ አንዷት ብቻ ስለሆንኩ እነሱ አገለገሉኝ። እንደምታውቀው ረጅም ቀጭን አስቀያሚ ቢጤ ነኝ። ግን እስካሁን ያወቅኋቸው ወንዶች ልክ የውበት ንግስት እንደሆንኩ ያህል ተገዝተውልኛል። አገልግለውኛል። ብቻ ምን ልበልህ፤ በሄድኩበት እንደተገለገልኩ ነው። እና አሁን ያሲንን ማገልገል ለእኔ ሕይወት በቂ ነው (ሰባተኛው መልአክ ገጽ 38)።

> አልረሳውም። ልረሳው አልችልም። ልረሳው አልፈልግም። ሌሊት እመጣለሁ አልኩትና ሄጅ አልጋዩ ውስጥ ገባሁ። ልተወው ቆረጥሁ። ምናልባት አንድ ሰዓት ያህል ቆየሁ። ከዚያ በላይ ግን ልቆይ አልቻልኩም። እንደዚህ አላስችል ያለኝ እሱ ስለሆነ ብቻ ነበር ወይስ ሰው ሲገድል ስላየሁት ነበር? አላውቅም። የሆነው ሆኖ እሱ እዚያ ተጋድሞ እኔ እዚህ ሆኜ ልታገስ አልቻልኩም። ራቁቴን ወጣሁ። ሽቶ ተቀባሁ። ከመኝታዬ ወጣሁ። የእንግዳ ቤቱን መብራት አበራሁ (ትኩሳት ገጽ 208-209)።

ያሲን የተራኪው የምሥጢር ጓደኛ የመሆኑን ያህል ባህራምም ለተራኪው የልብ ጓደኛ ነው። ያሲንን ተራኪው በብዙ መንገድ የሚያደንቀውን ያህል ባህራምንም ያደንቀዋል። ያሲን ብዙ አዋቂ ተደርጎ የተሳለውን ያህል ባህራምም ብዙ ምሥጢራዊ እውቀቶችን (የካራቴ፣ የስለላ፣ የመረጃ) የተማረ መሆኑ ይገለጻል። ያሲን ሴት ማጫወት የሚያውቅበትን ያህል ባህራምም ወንዶችን ያጋደለች ሴትን በእጁ አድርጓል። ያሲን እንደተኛት እያወቀ ተራኪው አይሪንን (የያሲንን ፍቅረኛ) የተኛትን ያህል ባህራም እንደተኛት እያወቀ ኒኮልን (የባህራም ፍቅረኛ) ተራኪው ይተኛታል።

በዚህ ልክ ታሪኮቹ ተናበው ይመጡና መለያየታቸው የሚመጣው ያሲን ቀጫጫ፣ ሰውነቱ ላይ ጸጉር የሌለበት፣ ጡንቻ የሌለው ልስልስ ሲሆን ባህራም ደግሞ ጸጉራማ፣ ጡንቻ ያለው ሆነው ተስለዋል፡፡ በሌላ በኩል ያሲን ኮሙኒዝምን ቢያውቅና ቢወድም ቅሉ ኮሙኒስትነቱን የተወ ነው፡፡ ለሪቮሊዩሽን ፍላጎት የሌለው ይልቁንም ኮሙኒዝምን እንደ አንድአዲስ ኃይማኖት የሚያይ ነው፡፡ ባህራም ግን አሁንም ኮሚኒስት፣ አሁንም ኮሚኒዝምን የሚያነብ፣ ሪቮሉዩሽን ለማስነሳት ተግባራዊ ሥራን የሚሠራ ነው፡፡ ትኩሳት ሲጠናቀቅም ባህራም ሪቮሊዩሽን ለማስነሳት ሃያ ሚሊዮን የኢራን ዜጎችን ለመታደግ ቆርጦ ሲነሳ ይታያል፡፡ ይህ የሁለቱ ገጸ ባህርያት መለያየት ግን ተለያይቶ ተለያየ የማያሰኝ መሆኑን አጥኝው ያምናል፡፡ ይልቁንም ደራሲው ይሁነኝ ብሎ ያደረገው እንጅ፡፡ ባህራም ወደ ኢራን አቀና፤ ያሲንን ሆኖ ተመለሰ፡፡ አስቀድሞ በሪቮሊዩሽን ያምን ነበር፣ ነገር ግን ከኮሙኒስቶች ጋር መቀጠል አልቻለም፡፡ በትኩሳት ላይ እንደምናየው ባህራም ለስንት ዓመታት የደከመለትን ሪቮሊዩሽን በአንድ ምክንያት አልሳተፍም ሲል እናያለን፡፡ ‹‹ኒኮል ነፍሰ ጡር ናት፤ ልጃችንን ጥዬ አልሄድም›› በሚል ምክንያት፡፡ መልሶ ለሪቮሊዩሽን ፈቃደኛ የሆነው ጽንሱ የአንተ ሳይሆን የልዑል ሰገድ ነው የሚል ደብዳቤ ከኒኮል ሲደርሰው ነው፡፡ እናም በሰባተኛው መልአክ እውነትን ከግብረ ስጋ ውስጥ የሚፈልግ ‹‹ተመራማሪ›› ሆኖ ብቅ አለ፡፡

**‹‹አልጋ ወራሽ››**

የግብረ ገብ ፍልስፍናውን ለማሄድ የተለያዩ ገጸ በህርያትን የሚተርክልን የትኩሳቱ ተራኪ ከሰባተኛው መልአክ ተራኪ እምብዛም ለውጥ የለውም፡፡ ሲልቪ ከአሪን ጋር መሳ ለመሳ ሆና ተስላለች፡፡ ልኡል ሰገድ አየለን ተክቶ ለኢትዮጵያዊ ወኔ የሚሰዋ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዳኑ አየለ በሃፍረት፣ ልዑል ሰገድ በወንድነት ወኔ ሞቱ እንጅ፡፡ ትኩሳት የመጽሐፉን የማጠንጠኛ ቁም ነገር በጀምሽድ በኩል አንስቶ ይጠቁማል፡፡ ገጽ 159 ላይ ጀምሽድ ስለሕይወት ያለውን መረዳት እንዲህ ይገልጻል፤

> በመሰረቱ ሕይወት ግሩም ስጦታ ናት፡፡ ኑሮ ግን ይሰለቻል፡፡ ሀዘን ሞልቶበታል፡፡ ብስጭት ይበዛበታል፡፡ በሽታ ወሮታል፡፡ ሞት ደግሞ ይቆያል እንጅ አይቀርም፡፡ ስለዚህ መሞት ላይቀር እስኪሞቱ ደስታ ላይገኝ፣ ብስጭት ሊበዛ ለምን አሁኑኑ አንሞትም? ለምን ራሳችንን አንገድልም? ችኮ የሆነ ሀዘን፣ ብስጭት የወረሰው እውቀት ምኑ ይወደዳል? ራሳችንን የማንገድለው ሞትን ስለምንፈራ ብቻ ነው? ፈሪ ነን፡፡ በቃ ይኸው ነው (ገጽ 149)፡፡

ይህንን ጥያቄ የሚያነሳው ጀምሽድ ራስን ማጥፋት ጀግንነት መሆኑን ይናገራል፡፡ የሕይወት ትክክለኛ ግብም ራስን ማጥፋት መቻል ነው የሚል ዕይታ አለው፡፡ እንዳለውም አድርጓል፤ ልኡል ሰገድን አጥፍቶ ራሱን አጠፋ፡፡ ይህ እርሱ የጠየቀው ጥያቄ ግን የስብሀት የግብረ ገብ እይታን እንድናይ አነሳሽ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በዝክሩ ላይ ስብሐት እንደጻፈው ከገጸ በህርያቱ ውስጥ ራሱ ስብሀት የሚያደንቃቸው እንዳሉና ለምን እንደሚያደንቃቸውም ይናገራል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አብዮት ለማስነሳት የቆረጠው ባህራም ለቆራጥነቱ፣ ራስን ማጥፋት ነው ጀግንነት የሚለውን ጀምሽድን ለድፍረቱ፣ ከራሷ ጋር ታግላ ራሷን ያሸነፈችውን አማንዳ ለአሸናፊነቷ እንደሚያደንቃት ይገልጻል፡፡ ዳኑ እነዚህን ሁሉ አደንቃለሁ አለ እንጂ እቀበላለሁ አላለም፡፡ እሱ የሚቀበለው የያሲንን ቅደስና ነው፣ እሱ የሚያምነው በቆሻሻነት ክብር፣ እንዲሁም በብልግና ውበት ነው፡፡

በትረካው ውስጥ አንድም ሥፍራ ምን እንደሚማር፣ አስተማሪዎቹ ምን ዓይነት የማስተማር ዘዴን እንደሚጠቀሙ፣ ከትምህርቱ ምን እንዳተረፈ ወይም ምን እንዳጣ አልነገረንም። ብቻ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ መሆኑን ሆቴል ተከራይቶ እንደሚኖር ብቻ ጠቁሞናል። ይህ የሆነው ልዝብ የተረት ዛር ስለሰፈረበት መሆኑን በድህረ ታሪክ ዝክሩ ይገልጻል። እናም ሕይወትን በቁም ነገሯ በኩል የማየት ዝንባሌ እንደሌለው አፍታትቶ ሲናገር ኤኒያዊ የግብረ ገብ እይታውን ይበልጥ እያጸናልን ነው። ለተራኪው ትክክለኛው የግብረ ገብ መንገድ የራስን ደስታ መፈለግ ነው። ከዚያ ውጭ ያለው ትርፍ ነው። የሚከተለው ውይይት በተራኪውና በልዑል ሰገድ መካከል የተደረገ ነው፤

‹‹እውነት እንድወስድልህ ትፈልጋለህ?›› አለኝ።

‹‹አዎን። ግን ለህበሾቹ እንዳትነግር››

‹‹ግድ የለህም። እኔ ምልህ - የኔን ሸክም ደግሞ አንተ ብትሸከምልኝ። አውቃለሁ አስቀያሚ ነች። ግን ጠጋ ስትላት የደስ ደስ አላት። ደግሞ ከዚያች ቆንጆ ጋር ሰንብተህ ወደዚችኛዋ ስትመጣ ጥሩ ለውጥ ሳይሆን አይቀርም። ሞክር እስቲ››

‹‹አንተም ሞክር!›› (ገጽ 25-26)።

ከዚህ ውል በኋላ ስምምነታቸውን በመጨባበጥ ይገልጻሉ። የሥምምነቱ ዋነኛ ነጥብ ፍቅረኞቻቸውን መለዋወጥ ነው። በዚህ የግብረ ገብ እይታ መሰረት ጓደኛን እንደወንድም ማየት፣ የወንድምን ሚስት አለመመኘት፣ ወንድም የተኛውም ገላ ለመኘታ አለመመኘት የሚባሉ የግብረ ገብ እይታዎች ቦታ የላቸውም። እነዚህን እይታዎች የሚያስተምረው ኃይማኖት፣ ባህል ወይም ማህበረሰብ እዚህ ጋ ቦታ የለውም። የተራኪው የግብረ ገብ እይታ ኤኒያዊ ነውና፤ ይህ ኤኒያዊ የግብረ ገብ እይታ ደግሞ ‹‹የቆሻሻነት ክብር የብልግና ውበት›› ተብሎ የተጠቀሰው ነው። የባህል፣ የኃይማኖትና የማህበረሰብ ዕይታዎችን ደካማነት ለማሳየት በሰባተኛው መልአክ አስታጥቄ በትኩሳት ደግሞ ተካ እንዲያሳዩ ሆነው ተስለዋል። ታዲያ ሁለቱም በተራኪው ይወረፋሉ። ለምሳሌ ተካን እንዲህ ገልጾታል፤

ተካ ብሽቅ ነው እንጅ መጥፎ ልጅ አይደለም። እንዲያውም ልቡ በጣም ሰፊ ነው። ለምሳሌ አንድ ቀን ስናወራ ‹‹እኔ ሰው አውቆ ክፉ ይሰራል የሚባለውን አልቀበልም›› አለኝ ‹‹ማንም ሰው በጣም ክፉ የተባለው እንኳ ቢሆን ክፉ ሚሰራው ደግ የሰራ እየመሰለው ነው፤ ባለማወቅ

‹‹ሚስትህን ወይም እጮኛህን ቢያማግጥብህስ?›› አልኩት

‹‹አንተን ለመጉዳት አይደለም። ሴትዮዋን ሊደሰትባት ፈልጎ ነው እንጅ››

‹‹አሳብቆ ቢያጣላህስ?

‹‹ለክፋት ያለው አይደለም። ወይም ስብቀቱ ትልቅ ደስታ ስለሚሰጠው ነው። ወይም ስትጣሉ እሱ የተጠቀመ እየመሰለው ነው። ለክፋት ብሎ ክፋት አይሰራም። ባለማወቅ ባለማመዛዘን ነው›› (ገጽ 19)።

የተካ ብሽቅነት የተገለጸው ከላይ ባለው ውይይት ውስጥ ነው። ለክፋት ብሎ ክፋት አይሰራም ብሎ የሚሞግተው ተካ ብሽቅ ተብሎ ሲሳል ከጓደኛው ጋር ፍቅረኛ ለመቀያየር የሚመክረው

ተራኪው ግን ‹‹ብሽቅ›› ብሎ ሰዳቢ ሆኗል፡፡ ከዚህ ውጭ ተካ በተጠራ ጊዜ ሁሉ የአፉና የጫማው መሽተት፣ የቤቱ አለመጽዳትና ዝርክርክነቱ ናቸው የሚጠቀሱት፡፡ የዚህ ተምሳሌቱ ‹‹ባለህበት ሂድ›› ስልት የሚንንማለለው ባህላችን (ገጽ 255) መሆኑን አጥኚው ያምናል፡፡ ባለህበት ሂድ ተብሎ ከተገለጸው ባህላችን በተቃራኒ መቆምን የመረጠበትን መንገድ ሲገልጽም ኑሮ በጣም አጭርና ጣፋጭ በመሆኗ ለመኖር መሽቀዳደም ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ (ገጽ 42) በዚህ መሽቀዳደም ውስጥ የራስን ደስታ መፈለግ እንጂ ሌላ እውነት የለም የሚለው የተራኪው ፍልስፍና ነው፡፡ ከልዑል ሰገድ ጋር ፍቅረኛ መቀያየሩ በአማንዳ ጥንካሬ ያልተሳካ ቢሆንም፣ የሌላኛውን ጓደኛውን የተመስገንን ፍቅረኛ ሲልቪን በማማገጥ ‹‹ጣፋጭ ሕይወትን›› ማጣጣም ይቀጥላል፡፡

> አንች እንደፈልግሽ፡፡ ብትፈልጊ ተይውና እኔ ጋ ነይ፡፡ ብትፈልጊ ሳትነግሪው በድብቅ እንገናኝ፡፡ ብትፈልጊም የሚገባው ከመሰለሽ ነገሩን አስረጅው፡፡ እንደመሰለሽ አድርጊ (ገጽ 45)፡፡

ሁሉም አማራጭ ለእሱ ይሰራል፡፡ በሚያገኛት ጊዜ ደስታን ትስጠው እንጂ (ገጽ 45) ለጓደኛው ለተመስገን፣ ለወዳጅነት፣ ለይሉኝታ፣ ለባህል ለኃይማኖት ግድ የለውም፡፡ ሲልቪ ከፈለገች ተመስገንን ጥላው እሱ ጋ ትሁን፣ ከፈለገችም በድብቅ ይሁን፣ ከፈለገችም ከተመስገን ጋር ተደራድራ ‹‹የተሻለ ወሲበኛ›› ማግኘቷን ነግራው ትምጣለት፡፡ ዋናው የእሱ ደስታ ነው፡፡ በስተመጨረሻም ‹‹አልጋ ወራሽ›› (ገጽ 60) የሚባል ስያሜ ተሰጥቶት ከሲልቪ ጋር በአደባባይ ፍቅረኛ መሆኑን ያውጃል፡፡

የራስን ደስታ መፈለግ ልከኛው የግብረ ገብ መንገድ መሆኑን ማስረዳት ይቀጥላል፡፡ ‹‹ባህል›› ባለህበት እርገጥ ነው፡፡ ለለውጥ አይመችም የሚለው ተራኪው ‹‹ቅዱሱ ያሲን›› እውነትን ግብረ ስጋ ውስጥ እንደሚፈልገው ሁሉ እርሱም እውነትን ከብልግና ውበት ውስጥ ይፈልጋታል፡፡

> ‹‹ሰውየው ደስ አለኝ››
>
> ‹‹ስጋዊ ምኞት አሳደረብሽ?››
>
> ‹‹አዎን፡፡ በሀይል ተመኘሁት፡፡ ግን …››
>
> ‹‹ግን ምን?››
>
> ‹‹እሱ ራሱ በስጋው እንዲገናኘኝ አልፈለግኩም››
>
> ‹‹እግዲያውስ?››
>
> ‹‹አንተ እሱን ሆነህ እንድትተኛኝ ነው የፈለግሁት›› (ገጽ 85)፡፡

ይህ ውይይት በተራኪውና በሲልቪ መካከል የሚካሄድ ነው፡፡ ሲልቪ ራሷን መቆጣጠር እስኪያቅታት ድረስ የወሲብ ስሜት ያላት ሴት ናት፡፡ በመንገድ ላይ አንድ የሚያምር ወንድ ባየች ጊዜ ያንን ወንድ እያሰበች ከተራኪው ጋር መተኛት ትፈልጋለች፡፡ የዚህ አመክንዮ ምንም ያህል ያንን ያየችውን ብትወደው እሱን እያሰበች ግብረ ስጋ ማድረግ እንጂ ከእሱ ጋር መተኛት ፍላጎት እንደሌላት የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ በመንፈስ የተደረገ የሶስትዮሽ ወሲብ (ተራኪው፣ ሲልቪ ያ ያየችው ወንድ) በሰባተኛው መልአክ በሥጋ እውን ሆኖ በሦስት ሰዎች መካከል ግብረ ስጋ ሲደረግ ይተረካል፡፡

በትኩሳት ውስጥ ሲልቪ በተደጋጋሚ ወንዶችን እያየች ያየቻቸውንም እየተመኘች ከተራኪው ጋር ትተኛለች፡፡ ታዲያ ‹‹የቆሻሻነትን ክብር›› የሚወደው ተራኪው ከዚህ ውስጥ ደስታውን ሲፈልግና ሲያገኝ ያሳየናል፡፡ ከእሱ ጋር ተኝታ ከሌላ ወንድ ጋር በሃሳብ ስትገናኝ ‹‹አልቀፈፈውም›› እንዲያውም ይበልጥ ደስታን እየሰጠው መጣ እንጂ፤

> ከንፈሯ በሚያስጎመጅ አኳኋን ይርበተበታል (ምኞቱ ሲያሳብጠኝ ተሰማኝ፡፡ ታዲያ ከፍርሃት ጋር ነው፡፡ ምክንያቱም የተመኘኂት ቆንጆ ስለሆነች ብቻ ሳይሆን ሰውየውን ስትመኘው ስላየኂትም ነው?) (ገጽ 88)፡፡

ይቀጥልና ተራኪው በሚሰሩት የብልግና ስራ ውስጥ የበለጠ ደስታን እያገኘ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ይህ ከብልግና ላይ የሚገኝ ደስታ ‹‹እኤያዊ›› እንጂ ባህል፣ ኃይማኖት ወይም ሌላ አይነት ደንብና ሥርዓትን ያማከለ አይደለም፡፡ እንዲያውም በደምብና በሥርዓት ላይ ያመጸ እንጂ፡፡ ተራኪው የቆሻሻነትን ክብር እንዲህ ይገልጸዋል፤

> ተቃቀፍን፡፡ እንደ አንድ ቀኑ ሌሊት ተንገበገበች፡፡ ስስማት አፌ ውስጥ እያቃሰተች ጭኖቿን ከመጠን በላይ ፍርክክ አድርጋ አቀፈችኝ፡፡ ደምበኛው ፍቅር ሳይሆን ቆሻሻ ብልግና የምንሰራ መስሎ ተሰማኝ፡፡ የባሰ ቆሻሻ እንዲሆን አማረኝ (ገጽ 88)፡፡

በርግጥ የበለጠውን ‹‹ደስታ›› ለማግኘት የባሰ ቆሻሻ እየሆነ ሲሄድ ተራኪው ያሳየናል፡፡ በሀሳቧ ሌሎች ወንዶችን እያሰበች ከእሱ ጋር ትተኛ ከነበረችው ሲልቪ ጋር የበለጠ ቆሻሻ ለመሆን ይመክራሉ፤

> ‹‹እና ምን ትፈልጊያለሽ ንገሪኝ እስኪ?››
>
> ‹‹ትቆጣለህ!››
>
> ‹‹ይልቅ ንገሪኝ››
>
> ‹‹ተው!››
>
> ‹‹ንገሪኝ፡፡ ምን ያምርሻል?››
>
> ‹‹ወንድ ያምረኛል፡፡ ሶስት አራት ቆንጆ ቆንጆ ወንዶች ባገኝ እፈቅዳለሁ››
>
> ‹‹አንድ አይበቃሽም?››
>
> ‹‹አይበቃኝም፡፡ አልጠግብም፡፡ ዛሬስ አንተ እንኳ ብትሆን አታጠግበኝም››
>
> ‹‹እና ምን ይሻላል?››
>
> ‹‹አንተ ባትኖር መፍትሔ ነበረው››
>
> ‹‹እኔ ሳልኖር እንዲህ አይነት ስሜት ሲመጣብሽ ምን ታደርጊያለሽ?››
>
> ጠረጴዛ ላይ ያለውን ጥቁር ቦርሳዋን መታ እያረገች ‹‹ማስታወሻ ደብተሬ ውስጥ የቴሌፎን ቁጥሮች አሉኝ››

‹‹የወንዶች?››

ጭንቅላቷን በአዎንታ ነቀነቀች፡፡

‹‹አሁን ልትደውይላቸዋ ትችያለሽ እኮ›› (ገጽ 191)፡፡

በትንታኔው መጀመሪያ ያየነው የጀምሽድ የሕይወት ትርጓሜ በስብሐት ምላሽ እየተሰጠው ነው፡፡ ሕይወት ጥሩ ናት፤ ኑሮ ግን ይሰለቻል፤ ስለዚህ ራስን ማጥፋት ነው ጀግንነት የሚለው የጀምሽድ እይታ የለም ሕይወት ጣፋጭና አጭር በመሆኗ ለመኖር መሽቀዳደም ይገባናል በሚል ሙግት ይሞገታል፡፡ አጭርነቷን ለማሳየት፣ ጣፋጭነቷን ለማጠየቅ ስብሐት የመረጠው ዘዴ የደስታ አጣብቂኞችን መፍጠርና ያንን አጣብቂኝ ለማለፍ የሚወሰነውን ውሳኔ ማሳየት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ሲልቪ አስቀድሞ በመንፈስ ከሌሎች ጋር፣ በስጋ ግን ከእርሱ ጋር ትተኛ ነበር፡፡ የበለጠ ደስታን ፈለጉ፤ እናም በውስጧ የሚሰማትን እና የምትፈልገውን የደስታ አይነት ነገረችው፡፡ ከእሱ ጋር ከመተኛቷ በፊት ከሌሎች ሶስት አራት ወንዶች ጋር መተኛት እንደምትፈልግ ትነግረዋለች (ገጽ 191) አልከለከላትም፡፡ ከአራት ወንዶች ጋር እንድትተኛ ይልካታል፤ ታዲያ ከዚያ ስትመጣ ደግሞ ከእሱ ጋር እንደምትተኛ ያውቃሉ፡፡ ይሄንን የዋጋ አጣብቂኝ (Value Stuck) ፈትቶ ያሳየበት የስብሐት የግብረ ገብ ፍልስፍና ሆኖ በአጥኚው አይን ታይቷል፡፡ እነሆ አጣብቂኙ፤

> የሚያፈቅሯት ሴት ጥብቅ ያለ ሱሪ ለብሳ ሌላ ወንድ ፍለጋ ስትሄድ ማየት፣ ሄዳ ስትመለስ፣ ቢያንስ ቢያንስ ሶስት ወንድ በየተራ ሲደሰትባት፣ ሲስማት፣ ሲልሳት፣ ሲያለፋት ከቆየ በኋላ ከዚያ ተቀብለው ይሄንን ሁሉ እያወቁ ያችን የሚወዷትን ሴት ማቀፍ፣ መሳም፣ መላስ፣ በቅናት እየነደዱ ሴትዮዋን መተኛት - ይሄ ደግሞ ከሁሉ የጠለቀ፣ ከሁሉ የላቀ፣ ከሁሉ የደመቀ፣ ከሁሉ የጨለመ፣ የሚያቃጥል፣ የሚያበርድ፣ የሚያስደስት፣ የሚያበሳጭ፣ የሚገድል፣ የሚያድን፣ ከስሜት በላይ የሆነ ስሜት ይሰጥ ይሆን (ገጽ 191-192)፡፡

ይሄ ለቅጽበት ያመጣው የግብረ ገብ አጣብቂኝ ጥቂት ጊዜ ከእርሱ ጋር ይቆያል፡፡ ሲኒማ ገብቶ ፊልም አይቶ እስኪወጣ ድረስ ግን ተመልሶ በአእምሮው ሲመጣበት አልነገረንም፡፡ እንዲያውም ጉዳዩን ረስቶት እንደነበር ያነሳል፡፡ በውላቸው መሰረት ሲልቪ ከአራት ወንዶች ጋር ተኝታ ከቀጠሮ ሰዓቷ አርፍዳ ትመጣለች፤ እንደ አመጣጧ ተቀበላት፤ እናም እንዲህ ይላል፤

> ነገረችኝ፡፡ የሳሟትን፣ የላሷትን፣ የነከሷትን፣ ሁሉን አንድ ባንድ ነገረችኝ፡፡ የስሜቱ አዲስነት፣ ብዛት፣ ጥልቀትና ሃይል ካሰብኩት በላይ ሆነ፡፡ መጨረሻ ላይ ከስሜት ብዛት ስጮህ በእጇ አፌን አፈነች፡፡ በብዙ ለስላሳ ቃላት ‹አይዞህ ያንተ ነኝ›› እያለች አባበለችኝ፡፡ ገና ከላይዋ ሳልወርድ እንቅልፍ ወሰደኝ (ገጽ 195)፡፡

ይህ የበለጠ የመቆሸሽ ፍላጎት በፍላጎት ብቻ ሲቀር አይታይም፡፡ እንዲያውም ይበልጥ እየቆሸሸ ይበልጥ ብልግናው እየጨመረ ‹‹የብልግና ውበቱም›› ይበልጥ እየፈካ ሲሄድ እናያለን፡፡ እናም የስብሐት እኔያዊ የግብረ ግብ ፍልስፍና ቁልጭ ባለ ምስል ሲቀመጥ እናያለን፡፡

> አየሽ ማንም አልተኛሽ ማለት ያስፈራኛል፡፡ ጭለማ ውስጥ ነኝ ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ተኝቶኛል ብትይ ይሻለኛል፡፡ ግን አሁንም አንድ ሰው ደብቀሽኝ ሊሆን ይችላል፡፡ አራት ወንድ ተኛኝ ብትይ የበለጠ ይሻላል፡፡ ምክንያቱም የደበቅሽኝ

> *ነገር የለም። ስለዚህ መፍራት አያስፈልገኝም። ምክንያቱም የተወሰደብኝ ሁሉ ተመልሶልኝ አቅፌዋለሁ ማለት ነው* (ገጽ 199)።

**‹‹መንግስተ ሰማያት››**

በስብሐት እኤያዊ የግብረ ገብ እይታ የመጀመሪያው አንብሮ የመቆሸሽን ክብር መቀበል የብልግናን ውበት መለየት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ‹‹እንደ ያሲን ቅዱስ›› መሆን ነው። ያሲንን ቅዱስ ያሰኘው እውነትን ወሲብ ውስጥ የሚፈልግ ሰው መሆኑ ነው። ያሲንን ቅዱስ ያሰኘው ሌሎች በግብረ ስጋ ውስጥ ሊያዩ የማይችሉትን ደስታ እሱ የሚያይ በመሆኑ ነው። ያሲንን ቅዱስ ያሰኘው በአንድ አልጋ ሶስት ሆኖ መተኛቱ ነው። ያሲንን ቅዱስ ያሰኘው ሴትንም ወንድንም ለወሲብ የሚመርጥ ሰው በመሆኑ ነው። ይህ አንብሮ በትኩሳትም ውስጥ ይገለጻል፤ ታዲያ በባህራም አይደለም በራሱ በተራኪው እንጂ። ተራኪው ወሲብን እንደያሲን ሲጠበብበት፣ እዚህም እዚያም እዚችም እዚያችም ጋር ሲያደርገው ይነግረናል። በስም ከተጠቀሱ ሴቶች ከሁሉም ጋር ወሲብ ማድረጉን የሚነግረን ተራኪው ትረካው የወሲብን መንግስተ ሰማይነት የሚያብራራ ነው። ‹‹ያን ሰሞን አንዲት ቆንጆ አሜሪካዊት ነበረች። አይኗ ሰማያዊ፣ ጸጉሯ በጣም ንጹህ ቡና አይነት። እጅግ ደስ ትላለች። አልጋ ውስጥ ልብ ታጠፋለች›› (ገጽ 14) በሚል ከወሲብ ጋር ያለውን ቁርኝት የሚናገረው ተራኪው ብዙ ሳይቆይ ሲልቪን ከተመስገን አለያይቶ የግብረ ስጋን ቅደስና ይተርካል። ልዑል ሰገድ ተገድሎ መቀበሩ እንኳ ሳይነገር ምናልባትም በሰዓታት ውስጥ ልኡል ሰገድን ፍለጋ ከመጣች አማንዳ ጋር ያደረገውን ወሲብ ቅድስና ይናገራል ‹‹መኖሩን ሰምቸው የማላውቀው አዲስ የግብረ ስጋ አገር አሳየችኝ›› (ገጽ 225) ይላል። ሲልቪ የተመስገን፣ አማንዳ የልኡል ሰገድ ፍቅረኞች ነበሩ። የቀረችው የባህራም ፍቅረኛ ኒኮል ነበረች። ኒኮል የባህራም ፍቅረኛ ትሁን እንጂ ልዑል ሰገደም ጀምሽድም ደጋግመው ተኝተዋታል፤ እንዲያውም ተጋድለውባታል። ይሄኛውን የመደምደሚያ አድርጎ ያመጣውና እንደያሲን ቅዱስነትን ያብራራል፤

> *....ያች ልጅ መንግስተ ሰማያትን አጣጥፋ ጠቅላ በጭኖቿ ውስጥ ደብቃ ነው የምትዞረው ልልህ እችላለሁ። እኔ ምለው እንደ ኒኮል ያለች ሴት እየተኙ ሁለት አመት ኖረው ቢሞቱ ምናለበት? ቢሰነብቱ ትርፉ ማርጀት አይደለም? እርጅና መጥቶ አጥንቶቼን አኮራምቶ ጅማቶቼን ሸምቀቆ፣ ቆዳዬን አጨማዶ፣ አይኔን አጨናብሶ፣ ጠረኔን ሰርቆ፣ በቁሜ በኤክስ አሮጊቶችና ሽማግሎች ሽታ ከሚገንዘኝ ኒኮልዬ ጭኖች መሃል ገብቼ ሙቀቱ ውስጥ ቀልጬ፣ ርጥበቱ ውስጥ ሚሙቼ ጥፍት ብል እመርጣለሁ። የሰው ልጅ መጨረሻውን መምረጥ ቢችል፣ መጨረሻዬ ኒኮል ውስጥ ቢሆንልኝ እመርጣለሁ...* (ገጽ 253)።

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ግኝት ደራሲው የምግባር ፈላስፋ ነው የሚል አይደለም። ይልቁንም በሥራው ውስጥ ፍልስፍናዊ ይዘቶች አሉ የሚል እንጂ። በዚህም መሠረት ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር የእኤያዊ የምግባር ፍልስፍና ተከታይ ወይም አቀንቃኝ ነው የሚያሰኝ ግኝት ተገኝቷል። በመቆሸሽና በብልግና ውስጥ ያለውን ውበትና ክብር በመጽሐፎቹ ተርኳል። ይህ ግላዊ ነው። በኃይማኖት፣ በማህበረሰብ፣ በባህል የሚመሩ ወይም በእነዚህ ውስጥ ያደጉ እሴት አክባሪዎች ከመቆሸሽ ውስጥ ክብርን ከብልግና ውስጥ ውበትን የሚፈልጉ አይደሉም። ወይም ይሄንን የሚያደርግን ሰው እንደጤነኛ አይመለከቱም።

**በምግባር ፍልስፍና ውስጥ ግን ይሄ አንደኛው የግብረ ገብ እይታ ተደርጎ ይወሰዳል። አንድ ሰው የፈለገውን፣ ደስታ የሚፈጥርለትን ነገር የማድረግ ስልጣን አለው ከሚለው ጀምሮ እንዲያውም ይሄንን ማድረጉ ትክክል ነው የሚለው የምግባር ፍልስፍና እኔያዊ** (Ethical egoism) **ነው። ይህ የሥብሐት መገለጫ ስለመሆኑ በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል። ይህ ጥናት በሥነ ጽሑፍ ውስጥ ፍልስፍናን ለማፈላለግ የሞከረ ሥነ ጽሑፋዊ ጥናት ነው። በማጠቃለያው ለማለት እንደተሞከረው የጥናቱ መደምደሚያ ደራሲው ፈላስፋ ነው የሚል ግኝት አይደለም። ይልቁንም በሥራው ውስጥ ልዩ ዓይነት የግብረ ገብ ዕይታ አንጸባርቋል የሚል እንጂ። ይህ የግብረ ገብ ዕይታ ከግብረ ገብ ፍልስፍና ንድፈ ሐሳብ አንጻር ሲተነተንም ስብሐት የእኔያዊ ግብረ ገብ ፍልስፍና አራማጅ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ጥናት ከፍልስፍናም ይሁን ከሥነ ጽሑፍ መስኮች በመጻሕፍቱ ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ ጥሩ መነሻ እንደሚሆን አጥኚው ያምናል።**

## ማጣቀሻዎች


ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር። (2012)። *ትኩሳት* (11ኛ ዕትም)። *ወይንሸት ማተሚያ* ቤት፣ አዲስ አበባ።

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር። (2012/ 2009)። *ሰባተኛው መልአክ* (አራተኛ እትም)። አዲስ አበባ።

ጠና ደዎ። (2008)። *ሰው ግብረገብና ሥነ ግበረ ገብ ፡ የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ፣ አዲስ አበባ።

Frankena, W. K. (1973). *Ethics* (2nd ed.). Prentice-Hall.

Hobbes, T. (1996). *Leviathan* (R. Tuck, Ed.). Cambridge University Press. (Original work published 1651)

Miller, A. (2013). *An introduction to contemporary metaethics* (2nd ed.). Polity Press.

Rachels, J., & Rachels, S. (2003). *The elements of moral philosophy* (5th ed.). McGraw-Hill.

Rand, A. (1964). *The virtue of selfishness: A new concept of egoism*. Signet Book, New American Library.

Shafer-Landau, R. (2015). *The fundamentals of ethics* (3rd ed.). Oxford University Press.

Sidgwick, H. (1874). *The methods of ethics* (7th ed.). Macmillan.

Singer, P. (2011). *Practical ethics* (3rd ed.). Cambridge University Press.

Vaughn, L. (2016) *Doing ethics: Moral reasoning and contemporary issues* (4th ed.). W. W. Norton & Company.